ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ረቡዕ | 82ኛ ዓመት ቁጥር 081 ኅዳር 21 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ
ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ


# “ኢትዮጵያ ወደ ብልጽግና ለምታደርገው ጉዞ በይነ መረብ መልካም ዕድል ይፈጥርላታል”

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

**ዳግማዊት ግርማ**



ፎቶ - በፀሐይ ንጉሤ

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ወደ ብልጽግና ለምታደርገው ጉዞ በይነ መረብ መልካም ዕድል ይፈጥርላታል ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ተናገሩ፡፡ በኢትዮጵያ የበይነ መረብ ተጠቃሚዎች ቁጥር ከአምስት ዓመት በፊት ከነበረበት 19 ሚሊዮን በአሁኑ ወቅት ከ30 ሚሊዮን በላይ መድረሱንም ጠቁመዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ትናንት በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን አዳራሽ በተከፈተው 17ኛው ዓለም አቀፍ የበይነመረብ አስተዳደር ጉባኤ ላይ በመገኘት ባስተላለፉት መልዕክት እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ የበይነ መረብ ተደራሽነትን በማስፋፋትና የሳይበር ደህንነትን በማስጠበቅ ረገድ በርካታ ሥራዎችን እየሠራች ሲሆን በዚህ ሂደት ላይም ዘርፉ ለብልጽግና ጉዞዋ የሚፈጥርላትን መልካም ዕድል እንደ አዳጊ ሀገር እውቅና ትሰጣለች፡፡

ኢትዮጵያ በዲጂታል ቴክኖሎጂና ኢንፎርሜሽን ዘርፍ ፈጣን ለውጥ እያመጣች ስለመሆኑ የተናገሩት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፤ የበይነ መረብ አገልግሎት የበለጸገች ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ የተያዘውን የአስር ዓመት እቅድ ተግባራዊ ለማድረግ የሚኖረውን ፋይዳም አስረድተዋል።

በዘመነ ዲጂታል የበይነ መረብ ጠቀሜታ ዘርፈ ብዙ መሆኑን የገለፁት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በትራንስፖርት፣ በግብርና እንዲሁም በጤና እድገት ላይ ዘርፉ ያለውን አወንታዊ ድጋፍም አመላክተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በበይነመረብ አስተዳደር ጉባኤው ላይ የኢትዮጵያን የአይሲቲ እና የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ጉዞ በማጉላት ተጨባጭ እና ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ ሐሳቦችን እንዲያዘጋጁም አደራ ብለዋል፡፡

አፍሪካ ደህንነቱ የተጠበቀ የበይነመረብ አስተዳደር ሊኖራት ይገባል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የበይነ መረብ አስተዳደር በጠንካራ ፖሊሲ መደገፍ እንደሚገባውም አሳስበዋል ።

“ኢትዮጵያ ወደ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






## ዓለም በቀጣይ አስተማማኝና አካታች የዲጂታል ደህንነት እንደሚያስፈልጋት ተገለጸ

- በዓለም ላይ ሦስት ቢሊዮን ዜጎች የበይነ መረብ አገልግሎት ተጠቃሚ አይደሉም

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- ዓለም በቀጣይ አስተማማኝና አካታች የዲጂታል ደህንነት ያስፈልጋታል ሲሉ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ አንቶኒዮ ጉተሬዝ ገለጹ። በዓለም ሦስት ቢሊዮን ዜጎች የበይነ መረብ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዳልሆኑም አመላክተዋል፡፡

ዓለም በቀጣይ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የሸሬ ኃይል ማስተላለፊያ መስመር ጥገና በሁለት ቀናት ይጠናቀቃል

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- ከሽራሮ ሽሬ ከተማ የሚደርሰው የከፍተኛ ኤሌክትሪክ ኃይል መስመር ጥገና ሥራ በሁለት ቀናት ውስጥ እንደሚጠናቀቅ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኮሙኒኬሽን ኃላፊ ሞገስ መኮንን በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሰሜን ኢትዮጵያ በተካሄደው ጦርነት ጉዳት ከደረሰባቸው መስመሮች መካከል አንዱ በሆነው ከሽራሮ ሽሬ ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ኃይል መስመር ጥገና ለማጠናቀቅ ባለሙያዎች ጥረት እያደረጉ ይገኛል።

የሸሬ ኃይል ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ሽሬ ከተማ



አቶ ዑሑማን ሱሩር

## በደቡብ ክልል የምርት ብክነትን ለመቀነስ ለቅድመ ምርት ሥራ ልዩ ትኩረት ተሰጥቷል

- ከመኸር እርሻ 88 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይጠበቃል
- 22ሺህ ሄክታር መሬት በበጋ ስንዴ ለመሸፈን ታቅዷል

**ገመቹ ከድር**

አዲስ አበባ ፡- የምርት ብክነት ለመቀነስ በቅድመ ምርት ሥራዎች ላይ በትኩረት እየተሠራ መሆኑን የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የገጠር ክላስተር

በደቡብ ክልል ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








“የሰላም ስምምነቱን የሚቃወሙ ጽንፈኞችን ዓላማ ማክሸፍና ሴራቸውን ማጋለጥ ይገባል”

- አቶ ሲራክ አማረ (ወዲ ሻምበል)
የቀድሞ ሠራዊት አባል

ገጽ 3

# ከ250 ሺህ
## በላይ ተገልጋዮች ይጠቀሙበታል ተብሉ የሚጠበቅ የክፍያ ሥርዓት ይፋ ሆነ

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- ከ250 ሺህ በላይ ተገልጋዮች ይጠቀሙበታል ተብሎ የሚጠበቀው "ሳንቲም ፔይ" የተሰኘ የክፍያ ሥርዓት ይፋ ተደረገ። ሳንቲም ፔይ ባንኮች ለፖስ ማሽንና ለሶፍትዌር ግዥ የሚያወጡትን ወጭ በሀያ እጥፍ ይቀንሳል ተብሏል፡፡

በክፍያ ሥርዓቱ ማስተዋወቂያ መርሐግብር ላይ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ምክትል ዳይሬክተር ትዕግስት ሀሚድ እንደተናገሩት፤ መሰል ቴክኖሎጂዎች በዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመቅረፍና ሀገራዊ ግብን ለማሳካት ትልቅ ሚና ይጫወታሉ ብለዋል።

ምክትል ዳይሬክተሯ መንግሥት የዲጂታል ክፍያ ሥርዓቶችን ለማዘመን ከፍተኛ የማሻሻያ ሥራዎችን በመሥራት ላይ እንደሚገኝ ገልጸው፤ ይህንንም እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ሳንቲም ፔይ ፋይናንሻል ሶሉሽን ይዟቸው የቀረባቸው የዲጂታል ክፍያ ሥርዓቶች ዘርፉን ወደ ተሻለ ደረጃ የሚያሸጋግሩ መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

መተግበሪያዎቹ ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያውያን ወጣቶች መሠራታቸውን የገለጹት ምክትል ዳይሬክተሯ "ይህም እንደ ሀገር ዲጂታል ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ በሚደረገው ጉዞ ላይ እምቅ አቅም ያላቸው ብቁ ወጣት የቴክኖሎጂ ባለሙያዎች እንዳሉን ማረጋገጫ ነው።" ሲሉ ገልጸዋል።

የሳንቲም ፔይ ፋይናንሻል አክሲዮን ማኅበር ቦርድ ሰብሳቢ ፕሮፌሰር ዳንኤል ቅጣው በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያውያን የተሠራው የክፍያ ሥርዓቱ ሀገራችን ለዘርፉ የምታወጣውን የውጭ ምንዛሪ ያስቀራል።

እንደ ፕሮፌሰሩ ንግግር፤ ዓለማችን በሁሉም ዘርፍ ከዚህ በፊት ታይቶ በማይታወቅ መንገድ ከፍተኛ ውድድር ውስጥ ትገኛለች፤ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በቴክኖሎጂ በመቀየር ላይ ያለችና ወደ ፊትም የምትቀየር ስትሆን ይህን የተቀየረ ዓለም በድሮ አሠራርና ልምድ መቋቋም ከባድ ነው፡፡

ዓለም በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና በቴክኖሎጂ እየሮጠች በመሄድ ላይ እንደምትገኝ የገለጹት ፕሮፌሰር ዳንኤል፤ ከዓለም እኩል ካልተሄደ የዘመንን ተግዳሮት መቋቋም የሚቻል አይደለምና ቴክኖሎጂው ሀገርን ከዘመን እኩል ማራመድ የሚያስችል ነው ብለዋል።

ፕሮፌሰሩ በአሁኑ ወቅት አብዛኛዎቹ የገንዘብ ዝውውሮች በካርድ የሚከናወኑ መሆናቸውን በማንሳት፤ ከዓለም ጋር እኩል ለመጓዝ ሀገርን ከዘመን ጋር በቴክኖሎጂ ማራመድ እንደሚገባ አስረድተዋል።

ይህ የዲጂታል ክፍያ ሥርዓትም በኢትዮጵያ ደህንነት መረብ ኤጀንሲ የደህንነት ምርመራ ሰርተፊኬት ያገኘ ሲሆን፤ በዓለም አቀፍ ደረጃም፤ ደህንነቱ መረጋገጡንም ቦርድ ሰብሳቢው ጨምረው አስረድተዋል።

ባንኮችም ለፖስ የሚያወጡትን ዋጋ በ20 በመቶ በማሳነስ ትልቅ የውጭ ምንዛሪ ወጪን ማዳን እንደሚችሉም ተናግረዋል።

ተንቀሳቃሽ ፓስ ማሽኖቹ የውጪ ሀገራት የክፍያ ካርዶችን የሚቀበሉና የሚያስተናግዱ መሆናቸውንም የገለጹት ፕሮፌሰሩ፤ በቅርቡም ከአውሮፓ ባንኮች እንዲሁም ከ10 ሺህ በላይ የሆኑ የአሜሪካን ባንኮች ወደ ሥርዓቱ የሚገቡበት ሁኔታ ላይ የሚያስፈልጉ ቅድመ ንግግሮች በመጠናቀቅ ላይ መሆናቸውን አስረድተዋል።

የሳንቲም ፔይ የሞባይል መክፈያ ሲስተም ባንኮችን እና ቴሌ ብርን ጨምሮ የቢል ክፍያዎችን ያስተሳሰረና ዲጂታል ኢትዮጵያን ለማየት በምናደርገው ጥረት ውስጥ ትልቅ እርምጃን ወደ ፊት የሚያራምድ ነው ተብሏል።

እነዚህንም የክፍያ ሥርዓቶችን ከስድስት አጋር ባንኮች ማለትም ከአቢሲንያ ባንክ፣ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ ቡና ባንክ፣ አዋሽ ባንክ፣ አማራ ባንክ እና ብርሃን ባንክ ከይሙሉ እና ቴሌ ብር ጋር በመተባበር ተግባራዊ ማድረጉን ገልጿል።



# ኮሚሽኑ በክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች ተጨባጭ መረጃዎችን ለማግኘት መሥራቱን ገለጸ

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ባለፉት ጊዜያት ከትግራይ ክልል በስተቀር በሁሉም ክልሎች እና የከተማ አስተዳደሮች በመገኘት ተጨባጭ መረጃዎችን ለማግኘት መሥራቱን አስታወቀ፡፡

የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን አባል ዶክተር ዮናስ አዳዬ ኮሚሽኑ ከተቋቋመ ጀምሮ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ያከናወናቸውን ተግባራት በተመለከተ በሰጡት መግለጫ እንዳሉት፤ ባለፉት ጊዜያት ከትግራይ ክልል በስተቀር በሁሉም ክልሎች እና የከተማ አስተዳደሮች በመገኘት ተጨባጭ መረጃዎችን ለማግኘት ሲሠራ ቆይቷል፡፡

እስካሁን ባለው ጊዜም የሰሜኑን ጦርነት ጨምሮ በሂደቱ የተወሰኑ ችግሮች ቢያጋጥሙም የታቀዱ ሥራዎችን በተያዘላቸው ጊዜ ለማከናወን ሲንቀሳቀስ መቆየቱን አስረድተዋል፡፡

የኢትዮጵያ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል የነበረው ጦርነት በሌሎች ክልሎች ኮሚሽኑ የሠራቸውን ሥራዎች በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል እንዳይሠራ አድርጎት እንደነበር ገልጿል።

የተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ሀገራዊ ምክክሩ እንዲሳካ የሚያደርጉት ተነሳሽነት መልካም አጋጣሚ እንደሆነ ጠቅሰው፤ በተጨማሪም ምክክሩ የሰመረ እንዲሆን በምሑራን ብቻ የሚገታ ምክክር ሳይሆን ድምፅ ያጡ ወገኖች ድምፅ እንዲያገኙ በትኩረት እንደሚሠራ አመላክተዋል፡፡

# በትንሽ ካፒታል ትልቅ ደረጃ የደረሱ ሴት አርሶ አደሮች

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሃገራችን በምግብ ራሳችንን ለመቻል የሚደረገው ጥረት በተጠናከረ መልኩ ቀጥሏል፡፡ ከዚህም አልፎ በግብርናው ዘርፍ እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች ሃገራዊ ብልጽግናን ለማረጋገጥ በሚያስችል ቁመና ላይ ናቸው፡፡ ከዚህ ጎን ለጎንም በዘንድሮ ዓመት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያስጀመሩት የሌማት ትሩፋት አንዱ ተስፋ የተጣለበት የምግብ ዋስትናን የማረጋገጥ ስልት ነው፡፡

በቅርቡም የብልጽግና ሴቶች ሊግ በኦሮሚያ ክልል ቢሾፍቱ ከተማ የሌማት ትሩፋት በከተማዋ ባስጀመረበት ወቅት በመርሐግብሩ ላይ ያገኘናቸውና በትንሽ ካፒታል ተነስተው በከተማ ግብርና ትልቅ ደረጃ የደረሱ የሴት አርሶ አደሮችን ተሞክሮ ልናስቃኛችሁ ወደድን፡፡



ወይዘሮ ሙላቷ ገብረሥላሴ



ወይዘሮ ካሰች ማቶት

ወይዘሮ ሙላቷ ገብረሥላሴ የቢሾፍቱ ከተማ ነዋሪ ሲሆን በከተማው በሚገኘው በኢ.ፌ.ዴ.ሪ አየር ኃይል በጽዳት ሠራተኝነት ተቀጥረው ከእጅ ወደ አፍ የሆነ ኑሮን ይመሩ ነበር፡፡ በ1990ዎቹ አካባቢ ለፋሲካ በዓል በ90 ብር የገዙት ፍየል እርጉዝ በመሆኗ ፍየሏን በማቆየት በዓሉን በሌላ ነገር ለማሳለፍ ወሰኑ፡፡ ፍየሏ ወለደች፤ ባልጠበቁት ሁኔታ ግልገሎቿ ተባዙ፡፡ ያኔ ነው የከተማ ግብርና ሀሳብ በውስጣቸው ያደረው፡፡

ወይዘሮ ሙላቷ ፍየሎቹን በከፊል ወደ ሐበሻ ላም ቀየሩ፣ላሚቷም ወልዳ የላሞች ቁጥር እየጨመረ ሲመጣ ወይዘሮ ሙላቷ ላሞቹን ሸጠው ወደ ፈረንጅ የወተት ላሞች ቀየሩ፡፡ እንዲህ እያሉ ዛሬ ላይ ወደ አንድ ሚሊዮን ብር የሚጠጋ ሀብት አፍርተዋል፡፡

የወይዘሮ ሙላቷ ጓሮ ዞረን ተመለከትን፤ ሁሉም የአትክልት አይነት አረንጓዴ ካባ ደርበው ድህነትን የሚያስፈራሩ ይመስላሉ፡፡ የደለቡ በጎች ያስጎመጃሉ፣ ዶሮዎቹም ከአዳራሽ ያስካካሉ፣ ላሞቹም የተመልካቹን ቀልብ ይገዛሉ፡፡ በአጭሩ ከወይዘሮ ሙላቷ ጓሮ የተመጣጠነ ምግብ በአንድነት ያገኛሉ፡፡

ወይዘሮ ሙላቷ የተሻለ ገቢ ለማግኘት ብሎም ለዩኒቨርሲቲ ተመራቂው ለታላቅ ልጃቸው የሥራ እድል ለመፍጠር በአዲስ አበባ ሱፐር ማርኬት በመክፈት በልጃቸው አማካኝነት ምርታቸውን ለገበያ በማቅረብ ጥሩ ገቢ እያገኙ መሆናቸውን ነገሩን፡፡ ምርታቸውን ከቢሾፍቱ ወደ አዲስ አበባ ለማጓጓዝ የሚያግዛቸው መኪና መግዛታቸውንም እንዲሁ አክለው ነገሩን፡፡

ወይዘሮ ሙላቷ በትንሽ ካፒታል ተነስተው በጠባቡ ጓሮአቸዉ ላይ በዚህ ደረጃ ውጤታማ መሆን በወቅቱ የእሳቸውን ማሳ የጎበኙት የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ሳይቀር አግራሞትን የጫረና ለከተማ ግብርና ተስፋ ሰጪ ጅምር መሆኑን ለመመልከት ተችሏል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ በከተማ ግብርና አስደማሚ ውጤት ያስመዘገቡት ሌላኛው የቢሾፍቱ ከተማ ሴት አርሶ አደር ወይዘሮ ካሰች ማቶት ናቸው፡፡ ወይዘሮ ካሰች "ሀ" ብለው ወደ ከተማ ግብርና ሥራ ሲገቡ መነሻ ካፒታላቸው ከ10 ሺህ ብር የማይበልጥ ሲሆን ዛሬ ላይ የካፒታላቸው መጠን ከ 7 ሚሊዮን ብር በላይ ነው፡፡

የወይዘሮ ካሰች ጓሮ አትክልት፣ ዶሮዎችና ላሞች ብቻ ሳይሆን በፍራፍሬ አሸብርቋል፡፡ በተለይ እንደ ሀገር ችግር የሆነው የከብቶች መኖ በወይዘሮ ካሰች ጓሮ ተትረፍርፎ ይገኛል፡፡ "የዝሆን ሳር" የሚባለው ሳር በአንድ በኩል የከብቶች ቀለብ በመሆን በሌላ በኩል ደግሞ ቀዬውን የአረንጓዴ ግርማ ሞገስ በማልበስ ልዩ የውበት ገጽታን ይሰጣል፡፡

በወይዘሮ ካሰች ጓሮ ጎበኚዎችን ያስደመመው ሌላ ነገር የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ነው፡፡ ከብቶቹን የሚያልቡ፣ ቅቤን ከወተት የሚለዩ እንዲሁም የዶሮዎችና የከብቶች መኖ በደቂቃ የሚፈጩ ዘመናዊ ማሽኖች በአንድ ላይ ይገኛሉ፡፡

በጠባብ ቦታ በዚህ ደረጃ የደረሱ ሴት አርሶ አደሮቹ ሰፊ ቦታ ከተሰጣቸው ተዓምር መሥራት እንደሚችሉም አስገንዝበዋል፡፡ የሌማት ትሩፋትንም በተግባር ያሳዩ ምርጥ ተሞክሮዎች እንደሆኑ መገንዘብ ተችሏል፡፡

# በአላማጣ ከተማ ያሉ ትምህርት ቤቶች ወደ መደበኛ የመማር ማስተማር ሥራ ተመልሰዋል

ሞገስ ጸጋዬ


ፎቶ - በሣሙኤል ተስፋዬ


አቶ ፍቃዱ አለሙ


አቶ በርሄ ገሰሰ


መምህር ረዳ ሽበሽ

አላማጣ:- ከሁለት ዓመት በኋላ በአላማጣ ከተማ ያሉ የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ወደ መደበኛ የመማር ማስተማር ሥርዓት መመለሳቸውን የአላማጣ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽሕፈት ቤት አስታወቀ።

የአላማጣ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽሕፈት ቤት የመምህራን፣ ርዕሳነ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ቡድን መሪ ፍቃዱ ዓለሙ እንደገለጹት፣ በአላማጣ ከተማ አራት ሁለተኛ ደረጃና ስምንት አንደኛ ደረጃ በድምሩ አስራ ሁለት ትምህርት ቤቶች አሉ። ይሁንና በጦርነቱ ምክንያት ትምህርት ቤቶቹ ሙሉ በሙሉና በከፊል ወድመዋል፣ ይሁንና ባላቸው አቅም ትምህርት እንዲጀምሩ ተደርጓል።

እንደ አቶ ፍቃዱ ማብራሪያ ትምህርት ቤቶች የወደሙት ማስተማሪያ ሰሌዳ እስኪጠፋ ድረስ በመሆኑ ሙሉ በሙሉ ወደ መማር ማስተማሩ እንዲገቡ የመንግሥትና የኅብረተሰቡ ርብርብ ያስፈልጋል። ለመማር ማስተማሩ አስፈላጊ የሆኑ መሣሪያዎችም መሟላት አለባቸው። አካባቢው በጦርነት የቆየና ተማሪዎች ከትምህርት ገበታ ርቀው የቆዩ እንደመሆኑ ከትምህርት ገበታ የሚቀር ተማሪ እንዳይኖር ለማድረግም የትምህርት ንቅናቄ ያስፈልጋል። ስለሆነም ከወላጆች ጋር በመነጋገር ወደ ትምህርት ገበታቸው እንዲመለሱ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ስለመሆኑ ገልጸዋል።

የአላማጣ ሙሉ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር አቶ በርሄ ገሰሰ እንደገለጹት፣ ለሁለት ዓመት ያህል ዝግ የሆነ ትምህርት ቤት በመከፈቱ በኅብረተሰቡ ዘንድ ከፍተኛ ደስታ ፈጥሯል። ተማሪዎችም ወደ ትምህርት ገበታቸው ተመልሰዋል፣ በአሁኑ ወቅትም ስድስት መቶ አርባ ዘጠኝ ተማሪዎች ተቀብለን እያስተማርን ነው።

ከጥቅምት 21 ቀን 2015 ዓ/ም ጀምሮ የትምህርት እንቅስቃሴ ተጀምሯል ያሉት ርዕሰ መምህሩ፣ የምዝገባውን ሂደትና ትምህርት መስጠቱን ጐን ለጐን እያስኬድን ነው። ተማሪዎች ለመማር፣ መምህራን ለማስተማር እንዲሁም ቤተሰብ ልጆቻቸው እንዲማሩ ከፍተኛ ፍላጐትና ምኞት በመኖሩ ትምህርት ሲከፈት ሁሉም መደሰቱን ገልጸዋል።

የትምህርት ቤቱ ንብረት በጦርነት ስለወደመ መማር ማስተማሩ ላይ ችግር እየፈጠረ ነው ያሉት አቶ በርሄ፣ በቀጣይ ለትምህርት ቤቱ አስፈላጊ የሆኑ ቁሶች እንዲሟሉ ጠይቀዋል። ካለው ችግር የተነሳም አንድን እስክሪቢቶ ሦስትና አራት መምህራን በጋራ እየተጠቀሙ መሆኑን ገልጸዋል። ትምህርት ቤቱ በጀት ቢኖረውም ባንክ ዝግ በመሆኑ ችግሩን እንዳባባሰበት ይገልጻሉ። ትምህርት ቤቱ የሕዝብ በመሆኑ በሙሉ አቅሙ ሥራ እንዲጀምር የሕዝብ፣ የመንግሥትና የተለያዩ አካላትን ተሳትፎ እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል።

የአላማጣ ሙሉ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህር የሆነው መምህር ረዳ ሽበሽ እንደገለጸው፣ ረዘም ላለ ጊዜ ከተቋረጠ በኋላ ትምህርት ጀምረናል። ትምህርት ቤቱ በመከፈቱ ተማሪዎች ከፍተኛ ደስታ ተሰምቷቸዋል።

እንደ መምህሩ ገለጻ፣ ተማሪዎች ለመማር፣ መምህር ለማስተማር ከፍተኛ ጉጉት ቢኖርም የወንበር አለመኖር፣ የመጽሐፍ እጥረት መኖርና ትምህርት ቤቶች ለመማር ማስተማር ምቹ አለመሆናቸው እክል እየፈጠረ ነው።

# ክፍለ ከተማው በ90 ቀን እቅድ የሚከናወኑ የልማት ሥራዎችን አስጀመረ

ፋንታነሽ ክንዴ

አዲስ አበባ፡- በአራዳ ክፍለ ከተማ «አራዳን እንደገና» በሚል መሪ ሀሳብ በ90 ቀን እቅድ ለሚከናወኑ ሰው ተኮር የልማት ሥራዎች የማስጀመሪያ መርሐ ግብር በትናንትናው ዕለት ተከናውኗል።

በመርሐ ግብሩ ላይ በክብር እንግድነት የተገኙት የአዲስ አበባ ብልጽግና ፓርቲ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ መለሰ አለሙ እንደገለጹት፤ በ90 ቀን እቅድ የሚከናወኑ ሰው ተኮር የልማት ሥራዎች ከመደበኛ ሥራ በተጨማሪ የኅብረተሰቡን አንገብጋቢ ችግሮች ለመቅረፍ የሚከናወኑ ናቸው፡፡

በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ሕይወት ለማሻሻል እየተሠራ መሆኑን አስታውሰው፤ በየተቋማቱ ምቹና የተቀላጠፈ አገልግሎት አሰጣጥ እንዲኖር ለማስቻልም በትኩረት እየተሠራ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ከዚህ ቀደም በአምስት ክፍለ ከተሞች የተተገበሩ የ90 ቀን እቅድ ሥራዎች ውጤት በማስገኘቱ ሁለተኛ ዙር የ90 ቀን እቅድ ሰው ተኮር የልማት ሥራዎችን ወደ ማስጀመር መግባቱን ገልጸዋል፡፡

ወደዚህ እቅድ ከመገባቱ በፊት በክፍለ ከተማው ያሉ አንገብጋቢ ችግሮችንና አስቻይ ሁኔታዎችን የመለየት ሥራ መሠራቱን ጠቅሰው፤ ዜጎች በተቀመጠው ስታንዳርድ መሠረት አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ፣ መልካም አስተዳደርን ማስፈን፣ የሚስተዋሉ ብልሹ አሠራሮችን በመቀነስ የሕዝብን እንግልት መቀነስ የሚሉ ጉዳዮች ላይ በትኩረት መሠራት እንዳለበት ተለይቷል፡፡

በተጨማሪም ከዚህ በፊት የተጀመሩ የልማት ሥራዎችን በአነስተኛ ወጪ በአጭር ጊዜና በከፍተኛ ጥራት ተፈጽመው ለአገልግሎት እንዲበቁ ለማድረግ አቅጣጫ መቀመጡንም አመላክተዋል፡፡

የኅብረተሰቡን ኑሮ ለማሻሻል በሚሠሩ ሥራዎች የባለሀብቶች እገዛ አስፈላጊ መሆኑን ጠቅሰው፤ በሚከናወኑ መሰል ሥራዎች ላይ ተሳትፎ እያደረጉ ለሚገኙ ባለሀብቶችም ምስጋና አቅርበዋል፡፡


አቶ መለሰ አለሙ

የአራዳ ክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ሞላ ንጉሥ በበኩላቸው፤ ክፍለ ከተማው የኅብረተሰቡን የኑሮ ጫና ለማቃለል በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

አራዳ የአዲስ አበባ ከተማ የሁሉም ነገር መነሻ መሆኗን ያስታወሱት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ በተቃራኒው ደግሞ ብዙ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግሮች በከፋ መልኩ የሚገለጥበት አካባቢ ነው ብለዋል፡፡

ከተማ አስተዳደሩ ይህን ችግር ታሳቢ በማድረግ በየዓመቱ እቅድ በማቀድ ለተግባራዊነቱ ርብርብ እየተደረገ መሆኑን ጠቅሰው፤ ይህን ጥረት ወደውጤታማነት ከፍ ለማድረግ «አራዳን እንደገና» በሚል መሪ ቃል ሰው ተኮር የልማት ሥራዎችን ለማከናወን ወደ ተግባር መገባቱን አስታውቀዋል፡፡

በትናንትናው ዕለት የተጀመሩ መሠረተ ልማቶች በተያዘው በ90 ቀን እቅድ የሚከናወኑ የልማት ሥራዎች የማኅበረሰቡን ዘርፈ ብዙ ችግሮች ለማቃለል ትልቅ ሚና እንዳላቸው አመልክተው፤ ፕሮጀክቶቹ በተያዘው ጊዜ ውስጥ ተጠናቀው ለአገልግሎት እንዲበቁ ሁሉም ባለድርሻ አካላት የየድርሻቸውን ሚና እንዲወጡ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

G+4 እና G+6 የመኖሪያ ሕንጻዎች፣ የሸገር ዳቦና የአትክልት ማከፋፈያ ሱቆች፣ የስፖርት ማዘውተሪያ ቦታዎች፣ አደባባዮችና የመንገድ አካፋዮች በ90 ቀናት ተገንብተው ለአገልግሎት ይበቃሉ ከተባሉ የልማት ሥራዎች ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

# የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የሕዝቡን የልማት ፍላጎት ምላሽ እንዲሰጥ ማድረግ ይገባል

ውብሸት ሰንደቁ


ኢንጂነር ወንድሙ ሲታ

አዳማ፡- የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ለመንግሥትና ለኅብረተሰቡ የልማት ፍላጎት ምላሽ መስጠት የሚችልበት ደረጃ ላይ ማድረስ እንደሚገባ የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ያዘጋጀው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲ አፈፃፀም እና ቀጣይ አቅጣጫዎች ዐውደ ጥናት በትናንትናው ዕለት በአዳማ ከተማ ሲካሄድ የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ኢንጂነር ወንድሙ ሲታ እንደገለጹት፤ ሀገሪቱ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ዕድገት አማራጭ ሳይሆን ብቸኛ ምርጫ የሚሆንበት የዕድገት ምዕራፍ ላይ ትገኛለች፡፡ በዘርፉ ይህን ከግምት ውስጥ ያስገባ የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ነው ብለዋል፡፡

የተዘረጋውን የአሠራር ሥርዓትም የጋራ በማድረግ ወደ ተጨባጭ ለውጥ ማምጣት የሁላችንም ድርሻ ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ይህን ማድረግ ሲቻልም የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ለመንግሥትና ለኅብረተሰቡ የልማት ፍላጎት በቂ ምላሽ ለመስጠት በሚችልበት ቁመና ላይ እንዲገኝ እንደሚያስችልም ተናግረዋል፡፡

እንደ ሚኒስትር ዴኤታው ገለጻ፤ ዘርፉ በርካታ ከፍተኛ ሀብት የሚንቀሳቀስበት እና በርካታ ባለድርሻዎችን በአንድ ጊዜ ማሳተፍ የሚችል ነው፡፡ ይህን ከግንዛቤ ያስገባ የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት ጭምር ያስፈልጋል፡፡ በዚህም በባለድርሻዎች መካከልም ጠንካራ መስተጋብር በማስፈን በሂደት ተወዳዳሪ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ለመፍጠር ይረዳል፡፡

የዘርፉን ተወዳዳሪነት ለማጎልበት ዘመናዊ የአሠራር ሥርዓትን በመዘርጋትና የመረጃ ተደራሽነትን በማስፋት የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ይበልጥ ተወዳዳሪ ማድረግ እንደሚገባ ኢንጂነር ወንድሙ ገልጸው፤ በዚህም ዘርፉን ለመንግሥትና ለሕዝቡ የልማት ፍላጎት ተገቢውን ምላሽ የሚሰጥበት ቁመና ላይ ማድረስ እንደሚገባም ጠቁመዋል፡፡

መንግሥት የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን በአግባቡ በመምራት ሀገሪቱ ከዘርፉ ተገቢውን ጥቅም እንድታገኝ እየተሠራ ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ለዘርፉ በተሰጠው ትኩረት የ30 ዓመት ፍኖተ ካርታ እና የ10 ዓመት የኮንስትራክሽን ልማት ዕቅድ አውጥቶ እየሠራ መሆኑን አንስተዋል፡፡

በተዘጋጁት ፍኖተ ካርታዎች ላይም ከክልል እና ከሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ጋር የጋራ መግባባት ላይ መደረሱን ጠቁመው፤ ሆኖም የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው በርካታ ሃብት የሚንቀሳቀስበት እና ብዙ አካላት የሚሳተፉበት በመሆኑ ለሀገሪቱ ልማት እና ዕድገት ከዚህ የተሻለ ተገቢውን አስተዋፅዖ በሚያደርግበት ቁመና ላይ ማድረስ ተገቢ ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

እንደ ኢንጂነር ወንድሙ ገለፃ፤ በመላው ሀገሪቱ ለማስፈፀም የታቀዱ የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ መሠረተ ልማት ዝርጋታዎች የሚመሩበት ሥርዓት ቀልጣፋና ውጤታማ በማድረግ ዘርፉ ለኢኮኖሚው የሚያበረክተውን አስተዋፅዖ ማሳደግ የማይተካ ሚና አለው፡፡ ይህንንም ሥርዓት ለማረጋገጥ የሚያስችል የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲና የ10 ዓመት የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ አቅም ግንባታ ፕሮግራም በማዘጋጀት ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ተገብቷል፡፡

ኮንስትራሽን ኢንዱስትሪ ልማት ላይ ስኬትን ለማስመዝገብ ያለመው ዐውደ ጥናት ዘርፉ የሚመለከታቸውን የፌዴራል እና የክልል ከፍተኛ አመራሮች፣ የዩኒቨርሲቲ ማኅበረሰብ አካላት፣ የፋይናንስ ተቋማት፤ እንዲሁም በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ውስጥ ያሉ የሙያ ማኅበራት እና ሌሎች ተዋንያን ባሳተፈ መልኩ ተካሂዷል፡፡

# "የሰላም ስምምነቱን የሚቃወሙ ጽንፈኞችን ዓላማ ማክሸፍና ሴራቸውን ማጋለጥ ይገባል"

**- አቶ ሲራክ አማረ (ወዲ ሻምበል) የቀድሞ ሠራዊት አባል**



በመንግሥትና በሕወሓት መካከል የተደረሰው የሰላም ስምምነት ሁሉንም ዜጎች ተጠቃሚ የሚያደርግ ስለሆነ ለተግባራዊነቱ የሁሉንም ርብርብ ይፈልጋል ሲሉ የቀድሞ የመከላከያ ሠራዊት አባል አቶ ሲራክ አማረ (ወዲ ሻምበል) አስታወቁ። የሰላም ስምምነቱን የሚቃወሙ ጽንፈኞችን ዓላማ ማክሸፍና ሴራቸውን ማጋለጥ ይገባል ሲሉም አክለው ገልጸዋል።

በፌደራል መንግሥትና በሕወሓት መካከል የተደረገው የሰላም ስምምነት ከስኬት እንዲደርስም የፖለቲካ ፓርቲዎችና ሕዝቡ የበኩላቸውን ድጋፍ ሊያደርጉ ይገባል ያሉት አቶ ሲራክ የሰላም ስምምነቱ በሕዝቦች መካከል የቆየውን ያልተገባ ጥርጣሬ ለማንሳት አቅም ይሰጣል የሚል ትልቅ ተስፋ እንዳላቸውም አስረድተዋል። አክለውም ይህ ስምምነት ከዳር መድረስ የሚችለውም ሆነ በጦርነት የተዳከመው ኢኮኖሚ ማገገም የሚችለው ስምምነቱ መሬት ላይ መውረድ ሲችል እንደሆነም አመልክተዋል።

በጦርነት ላይ ዋናው ጉዳት የሚደርሰው በወታደሩና በሚዋጋው አካል ላይ ብቻ አይደለም፤ ይበልጡኑ ውጊያው መካከል ያሉ ሰላማዊ ሰዎች ከፍተኛ ጉዳት ይደርስባቸዋል። ሕወሓት ሰሜን ዕዝን በማጥቃቱ ምክንያት ተቀስቅሶ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በተካሄደው ጦርነት የሰው ሕይወት ጠፍቷል፤ አካል ጎድሏል፤ ንብረትም ወድሟል። በአጠቃላይ ጦርነቱ የሃገርን ሃብት በልቷል።

ይሁንና ጦርነቱን ለማስቆም በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ በተፈረመው የሰላም ስምምነት ሕወሓት ትጥቅ ለመፍታትና ለፌደራል መንግሥቱ እውቅና ሰጥቶና በሰላም ለመኖር መወሰኑ በጣም ትልቅ እፎይታ ነው። ከማንም በላይ በዚህ ስምምነት ተጠቃሚውም የትግራይ ሕዝብ ነው።

የሰላም ድርድሩ ተፈረመ ሲባል ኢትዮጵያውያኖች እያሳዩ ያሉት ፍቅርና ድጋፍ የሚገርም ነው። ትግራይን ዳግም ለመገንባትና ለማነጽ ከልባቸው ያላቸውን ፍላጎት ሲናገሩም እየተደመጠ ነው፡፡ ይሁንና ዛሬ በየዓለም አደባባዩ የሰላም ስምምነቱን ሲቃወም የሚስተዋለው ጥቂት ጽንፈኛ ዲያስፖራ ከሕዝብ ተዘርፎ በሄደው ሃብት ተጠቃሚ የነበረ ነው።

ጽንፈኞቹ ዲያስፖራዎቹ በትግራይ ሕዝብ ሞትና መከራ ሁልጊዜም አትራፊ ናቸውና አሁን ጥቅማቸው ስለቀረባቸው በየአደባባዩ ቢንከባለሉ የሚገርም አይደለም ሲሉም አስረድተዋል።

ይህንን ዓላማቸውን በማክሸፍ ለዓለም ኅብረተሰብ ማጋለጥ ይጠበቅብናል። በተለይ ደግሞ ትግርኛ ተናጋሪ የሆንን ሰዎች ከፍተኛ ኃላፊነት አለብን። እርግጥ ነው፤ አሁን ላይ የእነዚህ ጽንፈኛ ዲያስፖራዎች ቁጥር ተመናምኗል፤ ምክንያቱ ደግሞ እውነት እየደመቀች፤ ውሸታቸው እየኮሰመነ ስለመጣ ነው ሲሉም አክለው ገልጸዋል።

## የአርብቶ አደር የምግብና ሥርዓተ ምግብ ደህንነት ፕሮጀክት ይፋ ተደረገ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በአርብቶ አደር አካባቢ በአየር ንብረት ለውጥ ሳቢያ የሚከሰቱ ችግሮችን ለመቋቋም የሚያስችል የአርብቶ አደር የምግብና ሥርዓተ ምግብ ደህንነት ፕሮጀክት ይፋ ተደረገ፡፡

የፕሮግራሙ ማስጀመሪያ ትናንት በሱማሌ ክልል ጅግጅጋ ሲካሄድ፤እንደተገለጸውም ፕሮጀክቱ በአፍሪካ ቀንድ የምግብ ደህንነት ችግርን የመቋቋም አቅምን በመገንባት የሴቶች፣ የወጣቶችና የሕዝቡን የኑሮ ሁኔታ ማሻሻል ይችላል ተብሏል።

ፕሮጀክቱ የአየር ንብረት ለውጥን የመቋቋም አቅምን ከማሳደግ ባለፈ በአርብቶ አደር አካባቢ ዘላቂ ሰላም እንዲፈጠርም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው መሆኑም ተጠቁሟል። ፕሮጀክቱ አጠቃላይ የአርብቶ አደሩን ሕይወት በማሻሻል በአፍሪካ ቀንድ ሰላምና ደህንነት እንዲረጋገጥ ያስችላልም ተብሏል።

በምስራቅ አፍሪካ የአርብቶ አደሩን ምርታማነት ከማሳደግ አንጻርም ላቀ ያለ ሚና እንደሚኖረውም ተጠቁሟል። ፕሮጀክቱ ለስድስት ዓመታት የሚቆይ ሲሆን በሶማሌ፣ አፋር፣ ኦሮሚያ፣ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ እና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልል የተለያዩ ወረዳዎች የሚተገበር መሆኑም ተመልክቷል።

የአፍሪካ ልማት ባንክና የኢትዮጵያ መንግሥት ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ የሚሆን የገንዘብ ድጋፍ ማድረጋቸውም በሥነ -ሥርዓቱ ላይ ተገልጿል።

በመርሐ ግብሩ ማስጀመሪያ ላይ የግብርና ሚኒስትሩ ዑመር ሁሴን፣ የሱማሌ ክልል ርዕሰ መስተዳደር ሙስጠፌ መሐመድ፣ በአፍሪካ ልማት ባንክ የምስራቅ አፍሪካ ቀጠናዊ ልማትና የቢዝነስ አቅርቦት ምክትል ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አብዱል ካማራ ፣ ከፌደራልና ከክልል የተወጣጡ የሥራ ኃላፊዎች ተገኝተዋል።

## በደቡብ ክልል የምርት ብክነትን ለመቀነስ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አስተባባሪና ግብርና ቢሮ አስታወቀ። በቅድመ ምርት አሰባሰብ የሚስተዋሉ ማነቆዎችን ለመግታት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ መሥራቱንም ገልጸዋል ።

በክልሉ በምክትል ፕሬዚዳንት ማዕረግ የገጠር ክላስተር አስተባባሪና የግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ዑስማን ሱሩር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት ፤ በክልሉ የመኸር ምርት ብክነት ለመቀነስ የሚያስችል ለኅብረተሰቡ በቂና አስፈላጊው ግንዛቤ ተሰጥቷል ። ዝናብ ሳይዘንብ የደረሱ ምርቶች ቶሎ መሰብሰብ፣ በኮምባይነር የሚሰበሰቡ ምርቶች ከአካባቢው ኮምባይነሮች ማዘጋጀት እንዲችሉ ማድረግ እና ከባለፈው ዓመት ተሞክሮ በመነሳት የተሻለ ምርት አሰባሰብ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ዝግጅት የማድረግ ሥራ እየተከናወነ ነው።

ክልሉ በመኸር እርሻ አንድ ሚሊዮን 250 ሺህ ሄክታር መሬት በዘር ለመሸፈን አቅዶ ከአንድ ሚሊዮን ሄክታር በላይ በዘር በመሸፈን 88 ሚሊዮን ኩንታል ምርት እንደሚጠበቅ የጠቀሱት አቶ ዑስማን፤ በአሁኑ ሰዓት የደረሱ ሰብሎች እየተሰበሰቡ ሲሆን ምርቱም ከባለፈው ተመሳሳይ የመኸር ወቅት ጋር ሲነጻጸር በማሳና በምርት ብዛት ጭማሪ መኖሩን ጠቁመዋል።

እንደ ኃላፊው ማብራሪያ ፤ ምርት በደረሰባቸው አካባቢዎች በተለይም በስምጥ ሸለቆ አካባቢዎች ምሥራቅ ጉራጌ ፣ ደቡብ ሶዶ ፣ መስቃን ፣ ምሥራቅ መስቃን ፣ ማረቆ ወረዳዎች የስንዴና ጤፍ ምርት መሰብሰብ ሂደቱ እየተጠናቀቀ ነው ።

በስልጤ ዞን ቆላማና ወይና ደጋ አካባቢዎች የሚገኙ ወረዳዎች ላምፉሮ ፣ ሚቾ ፣ ስልጥ፣ ምስራቅ ስልጥ፣ ዳሎቻ ፣ ሳንኩራ ፣ ኡልባራክ ምርት እየተሰበሰበ ሲሆን በአላባ በሦስቱም ወረዳዎች፣ በሀዲያና በወላይታ ስምጥ ሸለቆ አካባቢ የሚገኙ በጋሞና በጎፋ ቆላማ ቦታዎች በተመሳሳይ ሁኔታ ምርት እየተሰበሰበ ነው ብለዋል።

የቢሮ ኃላፊው፤ በጉራጌ ፣ ሀዲያ፣ ስልጤ ፣ ከምባታ፣ ወላይታ ፣ ጋሞ ፣ ጎፋ ደጋማ አከባቢዎች ሰብሎች እየደረሱ መሆናቸውን ገልጸው፤ ምርትና ምርታማነት ለመጨመር ከአንድ ሚሊዮን ኩንታል በላይ ማዳበሪያ ጥቅም ላይ መዋሉን ተናግረዋል።

የመኸር ሰብል ከተሰበሰበ በኋላ በአጠቃላይ 208 ሺህ ሄክታር መሬት በመስኖ በዘር ለመሸፈን ታቅዶ ወደ ሥራ የተገባ ሲሆን፣ ከእነዚህም 22 ሺህ ሄክታር መሬት በበጋ መስኖ ስንዴ ለመሸፈን እየተሠራ ነው ብለዋል። እስካሁን ባለው እንቅስቃሴ ከታረሰው 7ሺህ 600 ሄክታር መሬት 180 ሄክታር መሬቱ በዘር መሸፈኑን አመልክተዋል። የበጋ ስንዴ መስኖ እርሻ ሦስት ጊዜ ማረስ የቅርብ ተሞክሮ እንደመሆኑ መጠን ካለፈው ተመሳሳይ ጊዜ ጋር ሲነጻጸር በወጣቱ፣ በባለሀብቱ፣ በአመራሩና በአርሶ አደሩ ዘንድ ጥሩ መነቃቃትን ፈጥሯል ብለዋል።

በተመሳሳይ ዜና በክልሉ የተተከሉ አራት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ችግኞች ተጨማሪ መሬት ለመጠቀም፣ ምርትና ምርታማነት ለመጨመርና የሥራ እድሎችን በመፍጠር ላይ እንደሚገኝ ቢሮ ኃላፊው አያይዘው ገልጸዋል ። አብዛኞቹ ችግኞች የተተከሉት በተፋሰስ አካባቢ በመሆናቸው ውሃ አካላት ውሃ የመያዝ አቅማቸው በመጨመሩ ከአገልግሎት ውጪ የነበሩ መሬቶች ወደ መስኖ ልማት እንዲገቡ ትልቅ አስተዋፅዖ አበርክቷል ። አከባቢው ለመስኖ ምቹ መሆኑ ሴቶችና ወጣቶች ተደራጅተው የከብቶች መኖ በማልማት ለበርካታ ወጣቶች የሥራ ዕድል እየፈጠረ እንደሚገኝም ገልጸዋል።

ከአረንጓዴ አሻራ ጋር ተያይዘው የለሙ ፍራፍሬ ዛፍ ዓይነቶች በአሁኑ ሰዓት ፍሬ በመስጠት በኅብረተሰቡ ዘንድ ትልቅ መነቃቃትና የሥራ ባህሉንም እየቀየረ እንደሚገኝ የገለጹት አቶ ዑስማን፤ በተለይ በደቡብ ኦሞ አካባቢ የሚገኙ አርብቶ አደሮች ወደ ፍራፍሬ ልማት እንዲገቡ ግፊት እያደረገ መሆኑን ጠቅሰዋል ።

የሚመረቱ ፍራፍሬዎች ለሀገር ውስጥና ለውጪ ሀገር ገበያ ሰፊ ግብዓት የሚሆኑበት ሁኔታዎች በመታየት ላይ እንደሚገኝ ገልጸው ኅብረተሰቡ የተጀመረውን አረንጓዴ ልማትና ቅድመ ምርት መሰብሰብ ሥራውን ውጤታማ ለማድረግ የበኩሉን አስተዋጽዖ እንዲያበረክት ጥሪ አቅርበዋል ።

## "ኢትዮጵያ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ኢትዮጵያ በኮቪድና በሌሎች ሰው ሠራሽ ችግሮች በተፈተነችበት ወቅት ሥራን በበይነመረብ ማካሄድ መቻሏን በመልካም ጎን ያነሱት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፤ በዚሁም ልክ ዘርፉ የተሳሳቱ መረጃዎችን በማሰራጨት ሀገሪቷን ሲጎዳ መክረሙን ተናግረዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በይነ መረብ በርካታ በጎ ነገሮች ቢኖሩትም የተዛባ የመረጃ ስርጭትን በማስፋፋት ረገድም አሉታዊ አስተዋፅዖ እንዳለው ነው ያሰመሩበት። ኢትዮጵያ ባለፉት አራት ዓመታት ትክክለኛ ባልሆኑ የመረጃ ስርጭት ምክንያት ጫና ውስጥ እንደነበረችም ጠቅላይ ሚኒስትሩ በንግግራቸው አመላክተዋል።

ሀገሪቷ ያላትን የሕዝብ ቁጥር ያማከለ የበይነ መረብ ተደራሽነት ለማሳደግ በሠራችው ሥራ ብዙ ለውጦች አምጥታለች ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፤ በኢትዮጵያ በፈረንጆቹ የጊዜ ቀመር በ2017 ከነበረው 19 ሚሊዮን ተጠቃሚዎች በ2022 ከሠላሳ ሚሊዮን በላይ ተጠቃሚ መድረሱንም ገልጸዋል።

ከትናንት በስቲያ ጀምሮ በአዲስ አበባ እየተካሄደ ያለው 17ኛው የበይነ-መረብ አስተዳደር ጉባኤ ከበይነ መረብ ጋር ተያይዞ የሚመጡ ችግሮች ለመፍታት የሚያግዙ የመፍትሔ ሀሳቦች የሚንሸራሸሩበት ይሆናል የሚል ተስፋ እንዳላቸውም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ገልጸዋል።

## የሸሬ ኃይል ማስተላለፊያ መስመር ጥገና...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ከዚህ ቀደም ከሠራው ከፍተኛ የጥገና ሥራ መካከል ከሁመራ ወልቃይት ተከዜ-አዲጎሹ-ሽራሮ ድረስ ያለው የጥገና ሥራ ማጠናቃቃችን አንዱ ውጤት ነው ያሉት አቶ ሞገስ፤ በመጪዎቹ ሁለት ቀናት ውስጥ ደግሞ እስከ ሽሬ ድረስ ያለው የከፍተኛ ኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ መስመር በማጠናቀቅ የመልሶ ግንባታውን ሥራ እናጠናክራለን ሲሉ አስረድተዋል።

የሽሬ አካባቢ ኤሌክትሪክ የሚያገኘው ከተከዜ ጣቢያ በመሆኑ ከሽራሮ ሽሬ ካለው መስመር ጎን ለጎን ወደተከዜ የሚሄደውም ሆነ ወደሌሎች አቅጣጫዎች የሚሄደው የኃይል ማስተላለፊያ መስመር ጥገና እንደሚደረግለትም ገልጸዋል።

ከሁመራና ወልቃይት የሚመጣው የኤሌክትሪክ መስመር ላይ ከፍተኛ ችግር አጋጥሞት እንደነበር ያስታወሱት አቶ ሞገስ የሽሬ ኃይል መስመር ለሌሎች አካባቢዎችም የኤሌክትሪክ አገልግሎት ዳግም እንዲያገኙ ለሚደረገው ጥረት ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን ጠቁመዋል።

እስከ ሽሬ ድረስ ያለው የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ መስመር ጥገና በሁለት ቀናት ውስጥ ሲጠናቀቅ ሥራው ሽሬን አልፎ ወደአክሱምና ዓድዋ ከተሞች የሚያልፈው የከፍተኛ ኃይል ማስተላለፊያ መስመር ጥገና ይከናወናል ሲሉ አቶ ሞገስ አስታውቀዋል።

ዳይሬክተሩ እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል በኩል በተከናወነ የፍተሻ ሥራ ከተከዜ ሽሬ እንዲሁም ወደአክሱም ዓድዋ ከተሞች የተዘረጉት ከፍተኛ ኃይል ማስተላለፊያዎች አዳጋች የሚባል የጎላ ችግር እንዳላጋጠማቸው ሪፖርት ቀርቧል።

በዚህ መነሻነት አካባቢዎቹ ኤሌክትሪክ የሚያገኙበትን መንገድ ለመፍጠር አስፈላጊው ጥረት እየተከናወነ ይገኛል። ሠራተኞች ሌት ተቀን አስፈላጊውን የፍተሻና የጥገና ሥራ እያከናወኑ ናቸው ብለዋል።

በከፍተኛ የኤሌክትሪክ ኃይል ጥገና ሥራ ላይ የቴክኒክ ባለሙያዎችንና የጉልበት ሠራተኞችን ጨምሮ በቀን እስከ 200 የሚደርሱ ሠራተኞች እየተሳተፉ መሆኑን አቶ ሞገስ ገልጸዋል።

ከሽራሮ ሽሬ እንዲሁም ወደሁመራና አክሱም እንዲሁም ዓድዋ የሚሄዱ ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ መስመሮችን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ጥገናቸውን ቢያከናውንም የስርጭት መስመሮች ደግሞ በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት በኩል ይከናወናሉ ሲሉ አቶ ሞገስ ተናግረዋል።

በጦርነቱ ምክንያት ጉዳት ያስተናገደውን የሽራሮ-ሽሬ ባለ 230 ኪሎ ቮልት የኃይል ማስተላለፊያ መስመር ለመጠገን በስድስት ቡድኖች የተዋቀረ የጥገና ቡድን ጥረት እያደረገ እንደሚገኝ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል መረጃ ያመለክታል።

## ዓለም በቀጣይ አስተማማኝና አካታች...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ዋና ጸሐፊው ኢትዮጵያ እያስተናገደችው በሚገኘው በ17ኛው ዓለም አቀፍ የበይነ መረብ ጉባኤ ላይ በዙም ታግዘው ባደረጉት ንግግር ዓለም ወደፊት ደህንነቱ የተረጋገጠ የጋራ ተጠቃሚነትን ያማከለ የዲጂታል ደህንነት ያስፈልጋታል።

የጋራ ተጠቃሚነት ላይ የተመሠረተና የሳይበር ደህንነቱ የተረጋገጠ የበይነመረብ ግንኙነት ለሁሉም ዜጋ እንደሚያስፈልግ የገለጹት ጉተሬዝ፤ በተለይም ለአፍሪካ አስተማማኝና አካታች የዲጂታል ደህንነት መተግበር ያስፈልጋታል ብለዋል፡፡

ዋና ፀሐፊው እንዳሉት፤ አስተማማኝ የበይነ መረብ ዝርጋታን በዓለም ላይ ለማዳረስ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል። ምክንያቱም በዓለም ሦስት ቢሊዮን ሰዎች የበይነ መረብ አገልግሎት ተጠቃሚ አይደሉም፡፡ ስለሆነም እነዚህን ተጠቃሚ ማድረግ የቀጣይ የቤት ሥራ ሊሆን ይገባል፡፡

በተባበሩት መንግሥታት የአፍሪካ ኢኮኖሚክስ ኮሚሽን ተጠባባቂ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አንቶኔዮ ፔድሮ፤ አፍሪካውያን ግልጽና አካታች የዲጂታል ስትራቴጂ በመንደፍ ሁሉን አቀፍ አህጉራዊ ብልጽግናንና ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ በትብብር መሥራት እንደሚገባቸው ገልጸዋል፡፡

አንቶኒዮ ጉተሬዝ፤ ሁሉን አቀፍ የሆነ ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን ለማሳካት መረባረብ እንደሚገባ ጠቁመው፤ በአፍሪካ 871 ሚሊዮን ዜጎች ከበይነ መረብ ግንኙነት ውጭ ናቸው፤ እነዚህን ዜጎች በበይነ መረብ ማገናኘት በሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ማድረግ ይገባል ብለዋል፡፡

በጉባኤው የፖሊሲ አውጪዎችና ውሳኔ ሰጪዎች የተለያዩ አሠራሮችን መተግበር፣ የግልና የመንግሥት አጋርነት ማጠናከር አስፈላጊ ነው ያሉት ዋና ጸሐፊው፤ የበይነ መረብ ተደራሽነትን እውን ለማድረግ ያሉ ዕድሎችን መጠቀም ወሳኝ ነው ብለዋል ፡፡ ሲቪክ ማኅበራትና መንግሥታት ችግሮችን ለመቅረፍ በጋራ መሥራት እንዳለባቸውም አሳስበዋል፡፡

አፍሪካውያን የመሠረተ ልማት እጥረት፣ የዲጂታል አጠቃቀም ክህሎት ክፍተት፣ የፋይናንስ እጥረትና ሌሎች ችግሮችን ከየሀገራቸው ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማገናኘት ውጤታማ ሥራ ማከናወን አስፈላጊ ነው ሲሉም ገልጸዋል፡፡

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ጉዳዮች ምክትል ዋና ጸሐፊ ሊ ጁንሁዋ፤ በዓለም የዲጂታል ማኅበረሰብ ውስጥ አካል ሁሉንም የማኅበረሰብ ክፍል ደህንነት ያካተተ የበይነ መረብ ግንኙነት ሥርዓት በመዘርጋት በኩል ትልቅ ሥራን የሚጠይቅ ነው ብለዋል፡፡ የዲጂታል አብዮት በጅማሪ ላይ ያለባት አፍሪካ ግልጽና አካታች ስትራቴጂን በመንደፍ ልትሠራ እንደሚገባትም አስገንዝበዋል።

መንግሥታት ለዘርፉ የሚሰጡት ትኩረት፣ ዘርፉን በረጅም ጊዜ ኢንቨስትመንት መደገፍና የዲጅታል ዘርፉ ክህሎትን ማሳደግ የበይነ መረብ ተደራሽነትን ለማስፋት ወሳኝ ጉዳዮች መሆናቸውን አንስተዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የሰላም ስምምነቱ ትግበራ ምንም ዓይነት ቅድመ ሁኔታ የለውም!

ለሁለት ዓመታት ያህል በመንግስትና በሕወሓት መካከል ሲደረግ የነበረው ጦርነት ጥቅምት 23 ቀን 2015 በፕሪቶርያ በተካሄደው የሰላም ስምምነት ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን መሰረት አድርጎ ሉአላዊነትንና የግዛት አንድነትን ባከበረ መልኩ ዕልባት አግኝቷል፡፡ የተደረሰው ስምምነት ደም አፋሳሹን ጦርነት ለማስቆም፣ የርዳታ እና መሠረታዊ አገለግሎቶች ለማስጀመርና የአገሪቱን የድንበርና የግዛት አንድነት እንዲሁም ሕገ መንግስታዊ ስርዓት እንዲከበር የማድረግ አላማ አለው።

ህገመንግስታዊ ስርዓቱ ከኢፌዴሪ ህገ መንግስት የሚመነጭ ነው፡፡ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 102 በፌዴራልና በክልል የምርጫ ክልሎች ነጻና ትክክለኛ ምርጫ በገለልተኝነት እንዲካሄድ የማድረግ ስልጣን ያለው የምርጫ ቦርድ እንደሆነ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ሆኖም ከዚህ ድንጋጌ በተቃረነ መልኩ በትግራይ ክልል ‹‹ምርጫ ›› ተካሂዷል በሚል የትግራይ መንግስት መቋቋሙን ስሁት በሆነ መልኩ ለማወጅ መሞከሩ የሚታወስ ነው ፡፡ በወቅቱም የኢትዮጵያ መንግስት በትግራይ የተካሄደውን ‹‹ምርጫ›› እንዳልተካሄደ የሚቆጠርና የጨረቃ ምርጫ መሆኑን በመግለጽ ተቀባይነት እንደሌለው አስታውቆ ነበር፡፡

ይህንኑ ሃሳብ የሚያጸና ውሳኔ በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶርያ በተካሄደው ስምምነትም ሰፍሮ እናገኘዋለን፡፡ ምርጫው ህገ ወጥ በመሆኑም በትግራይ የሽግግር መንግስት ይቋቋማል፤ በሂደትም ምርጫ ተካሂዶ ክልሉን የሚያስተዳደር መንግስት ይጸናል፡፡ ስለሆነም አሁን ባለው ሁኔታ የትግራይ ህዝብን ሰላም የሚያስጠበቀውና ህጋዊ ውክልና ያለውም የፌዴራል መንግስት ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ በትግራይ ህዝብ ተመርጫለሁ የሚል ህጋዊ አካል የለም፡፡ ስለሆነም ከዚህ ውጭ የሚቀርቡ ጉዳዮች በፕሪቶርያው ስምምነት መሰረት ተቀባይነት የላቸውም፤ ሊቀመጥ የሚችል ቅድመ ሁኔታም የለም፡፡

በሌላ በኩል የፕሪቶርያው ስምምነት በግልጽ ካስቀመጣቸው ነጥቦች ውስጥ አንዱ በአንድ አገር ውስጥ አንድ መከላከያ ሰራዊት ብቻ መኖር አለበት የሚለው ነጥብ ነው፡፡ በስምምነቱ ላይ ዋነኛ ጉዳይ የሆነውን ትጥቅ ማስፈታትን በተመለከተ ሁለቱም ወገኖች በኢትዮጵያ ውስጥ አንድ የመከላከያ ኃይል ብቻ እንዳለ ከስምምነት ደርሰዋል። ስለዚህም ከተለያዩ አካላት የሚወጡ መረጃዎች እንደሚያመላክቱት ትጥቅ የማስፈታቱን ሂደት በጥሩ ሁኔታ ለማስኬድ እየተሰራ ይገኛል፡፡ ይህንን ሁኔታ የተለያዩ ቅድመ ሁኔታዎችን በማስቀመጥ ለማጓተት መሞከር አይችልም። በፕሪቶርያው ስምምነትም ሆነ በናይሮቢው የማስፈጸሚያ ሰነድ መሰረት ስምነቱን ወደ ተግባር ከመለወጥ ውጪ ሊቀመጥ የሚገባ ቅድመ ሆኔታ አይኖርም፡፡

ሌላው በፕሪቶርያው ስምምነት የፌዴራል መንግስትና ሕወሓት ውሳኔ ካሳለፉባቸው ጉዳዮች መካከል የኢትዮጵያን ሉአላዊነትና የግዛት አንድነትን የማስጠበቅ ስልጣን የኢትዮጵያ መንግስት ብቻ እንደሆነ በውል ሰፍሯል፡፡ በተለይም ከውጭው ዓለም ጋር የሚደረጉ ግንኙነቶችና ስምምነቶች ሁሉ ሊከናወኑ የሚችሉት በፌዴራል መንግስት ብቻ መሆኑ ከስምምነት ላይ የተደረሰበት ነጥብ ነው፡፡ ይህው ሃሳብም በህገ መንግስቱ አንቀጽ 51 ንኡስ አንቀጽ 8 ላይ በግልጽ ሰፍሮ ይገኛል፡፡

በአጠቃላይ የፕሪቶርያው ስምምነት የኢትዮጵያን ሉአላዊነትና የግዛት አንድነት የሚያጸናና የዜጎችን ሰቆቃ የሚቀርፍ ስምምነት በመሆኑ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የሚተገበር ነው፡፡ ስምምነቱ የኢትዮጵያን አንድነትና ሉዓላዊነት ከማጽናቱም ባሻገር በጦርነት ሰቆቃ ውስጥ የነበሩትን የትግራይ፤ የአማራና የአፋር ህዝቦችን እፎይታ አጎናጽፏል፡፡

ከፕሪቶሪያው ስምነት ቀጥሎ የተካሄደው የናይሮቢ ስምምነት መተማመንን የፈጠረና ኢትዮጵያ የጀመረችውን የሰላም መንገድ የሚያጸና ነው፡፡ በተለይም በጦርነቱ ምክንያት የተቋረጡ መሰረተ ልማቶችንና ሰብአዊ ድጋፎችን በሚፈለገው መልኩ ለማድረስ መሰረት የጣለ ነው፡፡ በዚሁ መሰረትም በትግራይና በአማራ ክልሎች አንዳንድ አካባቢዎች ተቋርጠው የነበሩ የቴሌኮሙኒኬሽን፤ የኤሌክትሪክና የባንክ አገልግሎቶች መልሰው ወደ አገልግሎት እንዲገቡ ለማድረግ አስችሏል፡፡ የሕዝቡን ችግር በፍጥነት ለመቅረፍም ሥራዎች በስፋት እየተሰሩም ይገኛሉ።

የፕሪቶሪያው የሠላም ስምምነት ምንም አይነት ቅድመ ሁኔታ እንደሌለውና በስምምነቱ መሠረት እንደሚፈፀምም የኢፌዴሪ የመንግስት ኮሚኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዶክተር ለገሰ ቱሉ መግለጻቸውም የሚታወቅ ነው።

በአጠቃላይ ለአገር ሉአላዊነትና የግዛት አንድነት መሰረት የሆነውና የዜጎች ሰቆቃ እንዲበቃ ያደረገው የፕሪቶሪያው ስምምነት ቅድመ ሁኔታ የለውም፤ ስለሆነም በስምምነቱ መሠረት መፈጸም ከሁሉም ወገን የሚጠበቅ ግዴታ ነው፡፡ ያለውም ብቸኛው አማራጭ ይሄው ብቻ ነው!


እፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73

ፋክስ 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፊያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

# አገርን እና ህዝቡን የሰረቀ የሚጣልበት ቅጣት ልክ በምን ይሰላል ...

**ሙሉቀን ታደገ**

የአውሮፓ ቅኝ ገዥ ኢፔሪያሊስቶችን በከፍተኛ ተጋድሎ ከአህጉረ አፍሪካ ያስወጡት አፍሪካዊያን ዛሬም ላይ አይለፍላችሁ ተብለው የተረገሙ ይመስላል። አፍሪካዊያን የአውሮፓ ኢፔሪያሊስቶችን ከአህጉራቸው ያስወጡ እንጂ ሰርተው ከማደግ ይልቅ በአቋራጭ ዘርፈው መክበርን በሚሹ የአፍሪካ ባለስልጣናት፣ ደላሎች እና ባለሃብቶች ክፉኛ እየተፈተኑ ኑሯቸውም ተመሰቃቅሎ ከአጋም የተጠጋ ቁልቋል ሆኖባቸዋል።

አሁን ላይ አፍሪካ በኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ኩነቶች ላይ እድገቶች እንዳይጎበኟት እና ምንም አይነት እንቅስቃሴ ማድረግ እንዳትችል እንደ ጎን ውጋት ቀስፎ የያዛት እና አንድም እርምጃ ወደ ፊት መሄድ እንዳትችል ጋሬጣ ሆኖ ከፊቷ የቆመው ስርቆት ወይም ሌብነት ነው። ይህም ሆኖ ግን ይህንን ደንቃራ አንድም ሰው በስሙ ለመጥራት የደፈረ አልተገኘም። ይልቁንም «ሙስና » እያሉ ያሽሞነሙኑታል እንጂ።

ስርቆት ስለምን ይሽሞነሞናል ? ሌብነት ሌብነት ነው! ስለምን የመንግስት አካላት ስልጣናቸውን ተጠቅመው ሲሰርቁ ሙስና የሚል የዳቦ ስም ይሰጠዋል ? ይህ ስህተት ነው። ሌባ ... ሌባ ነው ! ግለሰብ ሲሰርቅ ሌባ፤ ባለስልጣን ሲሰርቅ ሙስና የሚባል ስም ሊሰጠው አይገባም!

የህግ የበላይነት በአንድ አገር የሚረጋገጠው ባለስልጣናት እና ዜጎች በህግ ፊት እኩል ሲሆኑ ነው። ባለስልጣን ሲሰርቅ ሙስና ብሎ ማሽሞንሞን ዜጎች ሲርቁ ሌባ ማለት የህግ የበላይነትንም የዘነጋ አካሄድ ስለሆነ ሁሉንም ሌባ አልያም ሁሉንም ሙሰኛ ብሎ መጥራት ያስፈልጋል። እንደኔ ግን ሌባን ... ሌባ ! ብሎ መጥራቱ ብቻ እና ብቻ አዋጭ ይመስለኛል።

ለእኔ ! ቅኝ ገዥዎች እና ሌቦች (ሙሰኞች) ሁለቱም አንድ ናቸው። ሁለቱም አገርን ዘርፈው እና አመንምነው ይገድላሉ። ሁለቱም ሁሉንም ነገር ለራሳቸውና ለራሳቸው ጥቅም ብቻ ማዋልን ይፈልጋሉ። እነሱ ካጠገቡ ሌሎች በርሃብ እና በችግር ቢሞቱም ደንታቸው አይደለም።

የሌብነት ጥሩነት ባይኖረውም የአፍሪካ ሌባ ባለስልጣናት የስርቆት አካሄድ ግን እጅጉን ግብዝነት የሚስተዋልበት በመሆኑ ዜጎችን ከማራቆት በዘለለ የአንድን አገረ መንግስት ካስማ እና ማገር የሚሰባብር እና አገርንም የሚያፈርስ ነው። ይህን ስል በዓመክንዮ እንጂ እንዲሁ በግብዝነት ስላለመሆኑ በርካታ ማሳያዎችን መጥቀስ ይቻላል። ነገር ግን ከሚኖረን ጊዜ አንጻር ሁሉንም መጥቀስ ስለማይቻል የሞቡቱ ሴሴኮን ሌብነት እና የዛየርን እጣ ፈንታ በወፍ በረር ላስመለከትቻሁ ወደድኩ።

የበፊቷ ዛየር የአሁኗ ኮንጎ የአፍሪካ ብሄርተኝነት ምልክት የሆነውን የመጀመሪያውን የኮንጎ ጠቅላይ ሚኒስትር ፓትሪስ ሉሙምባን በሴራ አስገድሎ ወደስልጣን የመጣው ሞቡቱ ሴሴኮ አገሩን ዘርፎ በዓለማችን ቱጃሮች ተርታ መቀመጥ የቻለ አፍሪካዊ መሪ ነው። ቅንጡ መኪና፣ መነጻር፣ ሽቶ፣ አልባሳትን ወዘተ መግዛት መታወቂያው ነበር።

በወቅቱ ዛየራውያንም ቢሆኑ የአገራቸውን አንጡራ ሃብት የሰረቀውን ሞቡቱ ሴሴኮን ከማውገዝ ይልቅ ሞቡቱ ሰርቆ ስለሚገዛቸው የቅንጦት እቃዎች ማውራት ይቀናቸው ነበር። በዛየር የነበረው የባለስልጣናት ስርቆት ለውስጥ እና ለውጭ ደላሎች በዛየር ኢኮኖሚ ላይ እንደፈለጉ መወሰን እንዲችሉ በሩን ከፈተላቸው።

በዛየር የኢኮኖሚ ላይ እንደፈለጉ መወሰን እንዲችሉ በር የተከፈተላቸው ሌቦች በስርቆት የሚያገኙትን ገንዘብ ለማግበስበስ በነበራቸው ውድድር የዛየርን አንጡራ ሃብት ተስማምተው መዝረፍ ተሳናቸው። በአልማዝ ማዕድን የምትታወቀውን ዛየርንም ለበርካታ ትናንሽ ኮንጎዎች ከፋፈሏት።

ይህም አልበቃ ብሏቸው ! እነኝህ ክፍልፋይ ኮንጎዎች እስከዛሬ ድረስ በማያባራ እና መውጫ በሌለው የእርስ በርስ ጦርነት ውስጥ ገብተው እንዲጨራረሱ ተፈርዶባቸዋል። በርሃብ እና በበሽታ የሚጎዳው የኮንጎ ህዝብ በጦርነት ከሚረግፈው በላይ ሆኗል። የዚህ ሁሉ መነሻ ምክንያት የሆነው ህዝብ የሰጣቸውን አደራ በዘነጉ የባለስልጣናት ስርቆርት (ሙስና ) ነው።

እንደኢትዮጵያ ባሉ አገራት ደግሞ ሌቦች መዝረፋቸው ብቻ አይደለም አገርን እየጎዳ ያለው። ይልቁንም ስለመስረቃቸው በመረጃ እና በማስረጃ ሲደረስባቸው ስርቆታቸውን ለመሸፋፈን ወይም ለማደባበስ ጎሳን እና ሃይማኖትን እንደ ሽፋን መጠቀማቸው ነው። ይህ አካሄድ በብሄር ብሄረሰቦች እና በተለያዩ ሃይማኖቶች መካከል ቅራኔ ከመፍጠር ባለፈ እስከደም መፋሰስ እንዳደረሰ በተደጋጋሚ አይተናል። ይህ አካሄድ በአፋጣኝ መላ ሊበጅለት የሚገባ እጅጉን አደገኛ እውነታ ነው።

ሌላው በኢትዮጵያ ከሚሰራው ሙስና ጋር ተያይዞ ማንሳት የምፈልገው ጉዳይ ሌብነት/ሙስና በሚሰሩ ሰዎች ላይ ከሚወሰደው እርምጃ ጋር የተያያዘ ነው። እደንሚታወቀው ሙስና የአገርን ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ይገድላል። ነገር ግን በአገራችን ሙስና በሰሩ ሰዎች ላይ የሚወሰደው እርምጃ አይደለም አገርን የገደለ ሰው ላይ የሚወሰድ እርምጃ ሊመስል ይቅርና አንድ ሰው በገደለ ሰው ላይ የሚወሰድ እርምጃ እንኳን አይመስልም።

ስርቆት አገርን እንደሚገድል ከታወቀና አንድ ባለስልጣን ወይም ደላላ ያለውን ኃይል ተጠቅሞ አገሩን የሚሰርቅ ከሆነ በመጀመሪያ ደረጃ ያ ባለስልጣን ወይም ደላላ አገር እየገደለ መሆኑን ሊታመንበት ይገባል። አገር ሲሞት ደግሞ በውስጧ ያለው ህዝብ አብሮ ይሞታል። ስለሆነም አገርን እና ህዝቡን የሰረቀ ሰው አገርን እንደገደለ ተቆጥሮ የሚጣልበትም ቅጣት በዚያው ልክ መሆን አለበት።

ለምሳሌ የ20 ሚሊዮን ብር ፕሮጀክት ቅርጥፍ አድርጎ የበላን ሌባ ሙስና በሚባል መሸፋፈኛ ስም በመስጠት ሁለት ዓመት ብቻ ታስሮ የሚፈታ ከሆነ ሌላ ባለስልጣንም 20 ሚሊዮን ብር በ20 ዓመታት ሰርቶ እንደማያገኝ ስለማያውቅ ሁለት ዓመት ታስሮ 20 ሚሊዮን ብር ማግኘትን ይመርጣል።

ከዚህ ይልቅ በሌቦቹ ላይ የሚጣለው ቅጣት የሌቦቹን ሰብአዊ ክብር/ስብእና ጭምር የሚነካ/በማህበረሰቡ ውስጥ አንገት የሚያስደፋ ደረጃ ላይ የሚደርስ ከሆነ ሌቦቹ እጃቸውን ይሰበስባሉ። አገርን ማቁሰል፣ ማቆርቆዝ እና አመንምኖ ከመግደል ይታቀባሉ።

ይህንን በቁርጠኝነት ማድረግ ካልተቻለ ግን በአገራችን የቱንም ያህል ስርቆትን ወይም ሙስናን ለማስቆም ኮሚቴዎች ቢቋቋሙ ሌቦችን እንዳይሰርቁ ሊያገድ አይችልም። ከስርቆት (ሙስና) ጋር ተያይዞ እንደ አገር ያለን ህግ ጠንከር ብሎ ሊሻሻልም ይገባል። ከእነ ቻይና እና መሰል አገራት ብዙ ተሞክሮዎችን ቢወሰድም መልካም ነው።

## ፍረዱኝ

# ‹‹ከ30 ዓመት በላይ ያለማነውን የአረንጓዴ ስፍራ ለወራሪዎች ተሰጥቶብናል››

አቤቱታ አቅራቢዎች

# ‹‹ወረዳ 14 ቦታው ባዶ ቦታ እንጂ ግሪን ኤሪያ አለመሆኑን ገልጾልኛል ››

የቦሌ ክፍለ ከተማ የመሬት ዝግጅት እና ማስተላለፍ ዘርፍ ኃላፊ

ሙሉቀን ታደገ

ከ15 ቀናት በፊት በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 የተፈጠረን ውዝግብ መሰረት በማድረግ በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል አንድ የምርመራ ዘገባ መስራታችን ይታወሳል ።

የዚህ የምርመራ ዘገባ መነሻም «የቦሌ ክፍለ ከተማ እና የወረዳ 14 የመሬት ልማትና አስተዳደር ጽህፈት ቤት ከህገወጦች ጋር በመተባበር ከ30 ዓመታት በላይ ያለማነውና ስንጠቀምበት የኖርነውን የአረንጓዴ ስፍራ ወይም ግሪን ኤሪያ ሊነጥቁን » ሲሉ የቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 ማዕድን እና ኢነርጂ ቁጥር አራት ነዋሪዎች ለዝግጅት ክፍላችን አቤት ማለታቸው ነበር ።

በመጀመሪያው የምርመራ ዘገባ እንደተገለጸው ውዝግብ ከተፈጠረበት ጉዳይ ጋር ተያይዞ ቀጣይ ክፍል የምርመራ ዘገባ እንደሚኖር እና በክፍል ሁለትም ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላትን ምን አሉ የሚለውን ይዘን እንደምንመጣ ቃል ገብተን ነበር። በገባነው ቃል መሰረትም ጉዳዩ ይመለከታቸዋል ያልናቸውን አካላት አነጋግረን ቀጣዩን ክፍል ዘገባ ይዘንላችሁ ቀርበናል ።

### ለመነሻ ከባለፈው ዝግጅት

የክፍል አንድን የምርመራ ዘገባ ያነበቡ እና የዛሬውን የምርመራ ዘገባ ለማንበብ ለሚጠባበቁ እንዲሁም የዛሬውን የምርመራ ዘገባ እንደ አዲስ ለሚያነቡ አንባቢያን ደግሞ እንደመነሻ እንዲጠቀሙት ለማድረግ በክፍል ሁለት ወደተዘጋጀው የምርመራ ዘገባ በቀጥታ ከመግባታችን በፊት ከአስራምስት ቀናት በፊት የሰራነው የምርመራ ዘገባ ምን ይመስል እንደነበር በወፍ በረር ልናስቃኛችሁ ወደድን።


በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 ልዩ ስሙ ገርጂ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ በማህበር ለተደራጁ የከተማዋ ነዋሪዎች ቤት ሰርተው እንዲኖሩ ለማድረግ መንግስት በ1983 ዓ.ም በርካታ ባዶ ቦታዎችን ለነዋሪዎች አስተላለፈ።

ተደራጅተው የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ከመንግስት ከተሰጣቸው ማህበራት መከካልም ዛሬ ላይ ውዝግብ በተነሳበት ቦታ የሚገኙት የማዕድን እና ኢነርጂ ቁጥር አራት ማህበር አንዱ ነበር ። ቦታው እስካሁንም ድረስ የማዕድን እና ኢነርጂ ቁጥር አራት ማህበር እየተባለ ይጠራል።

የማዕድን እና ኢነርጂ ቁጥር አራት ማህበር ነዋሪዎች ቦታውን ሲረከቡት እንደዛሬው የለማ እና የሁሉንም አይን የሚስብ ሳይሆን በቅጡ እንኳን መውጫ መግቢያ የሌለው እና ያለማ ነበር ። ቦታው ያለማ ስለነበር የአካባቢው ነዋሪዎች ለበርካታ ጊዜያት በተደጋጋሚ በሌቦች ከፍተኛ ዝርፊያ ሲፈጸምባቸው ነበር። የአካል ጉዳት የደረሰባቸውም ቁጥራቸው ቀላል እንዳልነበር የማህበሩ ነዋሪዎች በክፍል አንድ ገልጸውልናል።

በ1983 ዓ.ም መንግስት ለማዕድን እና ኢነርጂ ቁጥር አራት ማህበር የመኖሪያ ቤት ሲሰጥ ከመኖሪያ ቤቱ በተጨማሪ የአካባቢው ማህበረሰብ የሚገለገልበት የአረንጓዴ ስፍራን (ግሪን ኤርያ) ጨምሮ ነበር። ይህንን የአረንጓዴ ስፍራ የማህበሩ አባላት እስከዛሬ ድረስ እያለሙ እየተጠቀሙበት ይገኛል ።

ይሁን እንጂ ምክንያቱ በውል በማይታወቅ አግባብ በመስከረም ወር 2015 ዓ.ም ማንነታቸውን የማያውቋቸው የተለያዩ ሰዎች ወደ አረንጓዴ ስፍራው (ግሪን ኤርያው) አብዝተው ይመላለሳሉ። በዚህም ግራ የተጋቡት ማዕድን እና ኢነርጂ ቁጥር አራት ነዋሪዎች


BOLE SUB CITY ADMINISTRAATION OFFICE

የመደበኛ ይዞታዎች ካርታ ዝግጅት የስራ ሂደት

4126 18/6/12

ቁጥር ቦ/ክ/ከ/የ/ይ/አሰ/ጽ/ቤት/18 4996 /2012

ቀን 17/6/2012 ዓ.ም.

ለመሬት ልማትና ከተማ ማደስ ጽ/ቤት
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- በአሲቲ ፓርክ ልማት ተነሺ የሆኑ ባለይዞታዎችን በተመለከተ በዴስኩ በኩል የተሰጠ ውሳኔ ሀሳብ ስለማሳወቅ፣

የቦሌ ክ/ከተማ የመደበኛ ይዞታዎች ካርታ ዝግጅት የስራ ሂደት አግባብ ያለው አካል ሳይፈቅድ የተያዙ ቦታዎችን ለማስተካከልና ለመከላከል በወጣው በመመሪያ ቁጥር 18/2006 መሰረት በልማት ምክንያት ተነሺ የሆኑ ባለይዞታዎችን መስተንግዶ እንድንሰጥ በቁጥር አአ/መልማቢ/01/1710/በቀን 10/10/06 እና ይአስ/848/07 በቀን 27/01/2007 እንዲሁም የመሬት ልመትና ማኔጅመንት ቢሮ ስለ የአርሶ አደር እና የአርሶ አደር ልጆችን መስተንግዶ አሰጣጥ በቀን 15/6/08 በቁጥር አአ/መልማቢ/01/2245/08 እና በቀን 11/8/10 በቁጥር ይአስ/2235/10 የካቢኔ ውሳኔ አቅጣጫ ተቀምጧል። በመሆኑም በመመሪያው በአንቀፅ 6 በንዑስ አንቀፅ 6.4 ከሚያዝያ 1997 አ/ም በፊት የተያዙ ስለመሆናቸው ቢረጋገጥም የከተማ ፕላንና የአካባቢ ሽንሻኖ የማይቀበላቸው ህጋዊ ባልሆነ መንገድ የተያዙ ይዞ ታዎች ተጣርቶ በሚቀርበው መረጃ መሰረት የግለሰቦችን ስም በዝርዝር በማደራጀት በደንቡ ላይ በተደነገገው መሰረት ምትክ ቦታ እንዲያገኙ ለመሬት ልማትና ከተማ ማደስ ጽ/ቤት እንዲተላለፍ ይደረግ በሚል ተገልጿል።

ይህንኑ መነሻ በአሲቲ ፓርክ ልማት ተነሺ ሆነው ከመሬት ልማትና ከተማ ማደስ ጽ/ቤት መረጃቸውን አደራጅተን እንድንልክ ዝርዝራቸው ከተላኩልን የልማት ተነሺዎች መካከል 1. ተመስገን መኮንን 2.ሰታ ጌቱ 3. ሀይሌ ጌቱ 4. ጌቱ አበበ 5. ብርሃኑ መኮንን 6.ሉሚ ጌቱ 7.የሱነሽ ጌቱ 8.አለሙ ጌቱ 9. አራ ጌቱ 10.እፍቱ መኮንን 11. የሮሰን መኮንን 12. ቤኛ መኮንን 13. ጫላ መኮንን 14. ኬኔ መኮንን 15.ፋንቱ መኮንን 16.ተስፋዬ መኮንን 17. ብርሃኑ ለማ 18. ታደለች መኮንን በዴስኩ በኩል የሚስተናገዱ ሲሆኑ መረጃ በማደራጀት በመመሪያ ቁጥር 18/2006 መሰረት ሊሰጣቸው የሚችለውን የቦታ መጠን ስፋት በመወሰን ያስተላለፍን መሆኑ ታውቆ የሊዝ ክፍያና የአገልግሎት ክፍያን በተመለከተ የመሬት ባንክና ማስተላለፍ ጽ/ቤት እና የይዞታ አስተዳደር ዴስክ በማስከፈል አገልግሎት መስጠት የሚቻል መሆኑን እንገልፃለን።

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ፡-
በቦሌ ክ/ከተማ አስተዳደር
- ለመሬት ይዞታ አስ/ጽ/ቤት
- ለመደበኛ ይዞታዎች ካርታ ዝግጅት
አዲስ አበባ

Bole Sub-City Administration Land ... Administration Office

☎+251 11/849 40 80
ለአዲስ ለውጥ በአዲስ መንፈስ
ጥላቻን በመቀነስ ፣ ያለንን በማካፈል ፣ ይቅርታን በማብዛት ፣ በፍቅር በመደመር ለለውጥ እንትጋ !!

ለቦታው ፀጉረ ልውጥ የሆኑትን ሰዎች ለምን ወደ ቦታው እንደሚመላለሱ ይጠይቋቸዋል። ሰዎችም ቦታውን ሊገዙ መምጣታቸውን ይነግሯቸዋል።

ይህን ተከትሎ የማዕድን እና ኢነርጂ ቁጥር አራት ማህበር ነዋሪዎች «ሻጩ ማን ይባላል ? »በማለት ቦታውን ለመግዛት የመጡ ሰዎችን ይጠይቃሉ። ገዥዎችም« አቶ ብርሃኑ መኮነን ደገፋ» የሚባሉ ሰው መሆናቸውን ተናግረው በቦታው ላይ የተሰራውን ካርታ ያሳያሉ።

ያልጠበቁት ነገር የገጠማቸው የማዕድን እና ኢነርጂ ቁጥር አራት ማህበር ነዋሪዎች ጉዳዩን ለማሳወቅ ወረዳ 14 ይሄዳሉ። ነገር ግን ስለጉዳዩ የሚያውቅ የወረዳ አመራር ሳያገኙ ይቀራሉ። ይህ በእንዲህ እንዳለ አረንጓዴ ስፋራው ላይ ስለተፈጠረው ችግር ለማስረዳት ወደ ክፍለ ከተማ መሬት ልማት እና አስተዳደር ጽህፈት ቤት ያመራሉ። የክፍለ ከተማው መሬት ልማት እና አስተዳደር ጽህፈት ቤትም ጉዳዩ ይመለከተዋል ስላለው የመሬት ማስተላለፍ ዘርፍ ለተባለው ክፍል ይመራቸዋል። ጉዳዩ የተመራለት የመሬት ማስተላለፍ ዘርፍ የተባለው ክፍልም ግሪን ኤርያው የእናንተ ስለመሆኑ ያላችሁን ማስረጃ ሁሉ ይዛችሁ ኑ ብሎ ያዝዟቸዋል።

የማዕድን እና ኢነርጂ ቁጥር አራት ማህበር ነዋሪዎችም በታዘዙት መሰረት ግሪን ኤርያው የእነሱ ስለመሆኑ ያስረዳልናል ያሉትን ሰነድ ሁሉ በመያዝ ወደ የመሬት ማስተላለፍ ዘርፍ ክፍል ቀረቡ ።

ሰነዱን ይዘው በመቅረብ ጉዳዩን ለመሬት ማስተላለፍ ዘርፍ ለተባለው ክፍል እያሳዩ ባለበት ወቅት ስለጉዳዩ ምን አይነት እውቅና እንዳልነበረው ሲነግራቸው የነበረው በቦሌ ክፍለ ከተማ የወረዳ 14 የመሬት ልማትና አስተዳደር ጽህፈት ቤት መሬቱን አቶ ብርሃኑ መኮነን ደገፉ ለተባሉ ሰው ወኪል ሊያስተላልፍ ሲሞክር ተገኘ። በዚህም የአካባቢው ነዋሪዎች እና በቦሌ ክፍለ ከተማ የወረዳ 14 የመሬት ልማትና አስተዳደር ጽህፈት ቤት መካከል አለመግባባት ተፈጠረ።

ይህን ተከትሎ ነዋሪዎቹ ጉዳዩን ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል በመያዝ «የቦሌ ክፍለ ከተማ እና የወረዳ 14 መሬት ልማትና አስተዳደር ጽህፈት ቤት የተሰራብንን በደል የኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት ተመልክቶ ፍርድ ይስጠን » ሲሉ ጥቆማ አደረሱን። ዝግጅት ክፍሉም ከጉዳዩ ጋር ተያይዞ በርካታ ምርመራዎችን አደረገ።

### የቀድሞው በቦሌ ክፍለ ከተማ የወረዳ 14 የከተማ ውበት እና አረንጓዴ ልማት ጽህፈት ቤት ምላሽ

የቀድሞው የቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 የከተማ ውበት እና አረንጓዴ ልማት ጽህፈት ቤት ኃላፊ የነበሩት አቶ አለማየሁ ፋፉ ይባላሉ። አቶ አለማየሁ ፋፉን ያነጋገርንበት ዋና አላማ ውዝግብ የተነሳበትን ቦታ በአረንጓዴ ስፍራነት ለማልማት በነበረው እንቅስቃሴ ከማዕድን እና ኢነርጂ ቁጥር አራት ማህበር ነዋሪዎች ጋር አካባቢውን ለማልማት በርካታ ደብዳቤዎችን ይጻጻፉ ስለነበር ነው ። አቶ አለማየሁ ስለጉዳዩ የሚከተለውን ብለውናል ።

አቶ አለማየሁ እንዳሉት፤ የከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ጽህፈት ቤት በማዕድን እና ኢነርጂ ቁጥር አራት በአረንጓዴ ስፍራነት ይለማ የነበረው ቦታ በአረንጓዴ ስፍራነት የተከለለ አልነበረም። ክፍት ቦታ ስለነበር ለከተማ ውበት እና ጽዳት ሲባል የቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 የከተማ ውበት እና አረንጓዴ ልማት ጽህፈት ቤት በጊዜአዊነት እንዲለማ የተደረገ ነው ።

ውበት እና ጽዳት ክፍት ቦታዎችን እንዲያለማ ኃላፊነት ለከተማ ውብትና አረንጓዴ ልማት ጽህፈት ቤት በመመሪያ የተደገፈ መብት ተሰጥቶታል የሚሉት አቶ አለማየሁ ፤ በዚህም ባዶ ቦታዎችን በማህበርም ሆነ ለባለሃብት በመስጠት በግዜአዊነት ማልማት እና ማስለማት እንደሚቻል ያስረዳሉ።

ይህን ተከትሎ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል በከተማ ውስጥ በየትኛውም አካባቢ የሚገኝን ክፍት ቦታ የከተማ ውብትና አረንጓዴ ልማት ጽህፈት ቤት እንዲለማ ማድረግ ይችላል ? መመሪያስ አለ ? ስንል ጠየቅናቸው። አቶ አለማየሁም ‹‹አዎ !› የሚል ምላሽ ከሰጡ በኋላ ስለመመሪያው እንዲህ ሲሉ አብራሩ፤ ‹‹ በከተማችን ውስጥ ባዶ ቦታዎች ሲኖሩ የከተማ ውብትና አረንጓዴ ልማት ጽህፈት ቤት እንዲያለማቸው የሚፈቅድ አዋጅ አለ። ማንኛውም ክፍት ቦታ የከተማን ውበት ለማስጠበቅ ሲባል በጊዜአዊነት እንዲለማ ይደረጋል። ይሄን አሰራር የሚፈቅደው አዋጅም አዋጅ 365/2011 እንደሚባል እና በዚህ አዋጅ ስር አንቀጽ 14 ላይም ስለባዶ ቦታዎች እጣ ፋንታ በግልጽ መቀመጡን ይናገራሉ።

በማዕድን እና ኢነርጅ ቁጥር አራት ስር የሚገኘውን የግሪን ኤርያ አይነት መሬት ላይ ካለው ነባራዊ ሁኔታ አንጻር ለልማት ተነሺዎች መስጠት ይቻላል ? ተብለው የተጠየቁት አቶ አለማየሁ ‹‹አዎ›› የሚል ምላሽ ሰጥተዋል። አቶ አለማየሁ አክለውም አይደለም የግሪን ኤርያን ይቅርና ነዋሪዎችም ተነስተው ቦታው ለልማት ሊውል እንደሚችል ነው የገለጹልን ።

ቅሬታ የተነሳበት ቦታ እርስዎ የወረዳ 14 ከተማ ውብትና አረንጓዴ ልማት ጽህፈት ቤት ኃላፊ በነበሩበት ወቅት ከእርስዎ መስሪያ ቤት ጋር በመተባበር በአረንጓዴ ቦታነት እየለማ ነበር ። ስለዚህ ምን ይላሉ ተብለው የተጠየቁት አቶ አለማየሁ ‹‹ቦታው አረንጓዴ ስፍራ አልነበረም›› ሲሉ መልሰዋል። የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍልም የእናንተ መስሪያ ቤትም ከአረንጓዴ ስፍራው ጋር ተያይዞ ቅሬታ ካነሱት የአካበቢው ነዋሪዎች ጋር የተላላካችኋቸው ደብዳቤዎች የሚያሳዩት ግን ቦታ በአረንጓዴ ቦታነት ሲለማ መቆየቱን ነው ። ስለዚህ ምን ይላሉ? ተብለው ለቀረበላቸው ጥያቄ። አቶ አለማየሁ ሲመልሱ ፤ የእነሱ መስሪቤት የጻፍነው ደብዳቤ ክፍት አረንጓዴ ቦታ የሚል እንጅ አረንጓዴ ቦታ የሚል አለመሆኑን ገልጸው፤ ይህ ቦታ በጊዜአዊነት እንዲለማ እንጂ ካርታ ስላልነበረው በጊዜአዊነት ሲለማ መቆየቱን ገልጸዋል።

የእናንተ መስሪያቤት ቦታውን ባዶውን እንዳገኘው ነው እየነገሩኝ ያለው። ቦታውን ባዶውን ነው ያገኛችሁት? ተብለው የተጠየቁት አቶ አለማየሁ ‹‹አዎ ! ቦታውን ባዶውን ነው ያገኘነው›› የሚል ምላሽ ሰጥተዋል። ይህን ተከትሎ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍልም ነዋሪዎቹ

# ፍረዱኝ

ግን ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ እንደአለሙት ይናገራሉ። ስለዚህ ምን ይላሉ? ሲል ጠየቀ ። አቶ አለማየሁም «ስለዚህ ጉዳይ የማውቀው ነገር የለም በማለት ምላሽ ሰተዋል »።

የማዕድን እና ኢነርጂ ቁጥር አራት ነዋሪዎች ለግሪን ኤርያው መብራት እና ውሃም እስከማስገባት የደረሰ ልማት ነው ያከናወኑት። ይሄን እንዴት ይመለከቱታል ? ተብለው የተጠየቁት አቶ አለማየሁ ፤ «ከመንግስት አካል መብራት እና ውሃ እንዲያስገቡ የፈቀደ አካል የለም» ሲሉ ይመልሰዋል። ይህ ተከትሎ መብራት እና ውሃ እንዲያስገቡ የተፈቀደበትን ከመብራት ሃይል እና ከውሃ ልማት መስሪያቤቶች ህጋዊ ደብዳቤ የተጻፈ ደብዳቤ አለ ብለን አሳየናቸው ። ስለዚህ ምን ይላሉ? ስንልም የጠየቅናቸው አቶ አለማየሁ « ስለዚህ ጉዳይ የማውቀው ነገር የለም» ሲሉ መለሱ።

**የቦሌ ክፍለ ከተማ የመሬት ዝግጅት እና ማስተላለፍ ዘርፍ ሃላፊ ምላሽ**

የቦሌ ክፍለ ከተማ የመሬት ዝግጅት እና ማስተላለፍ ዘርፍ ሃላፊ አቶ ጌታሁን ነጋሳ ይባላሉ ። የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍልም በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 ስለሚገኘው የማዕድን እና ኢነርጂ ቁጥር አራት ግሪን ኤሪያ ምን ያውቃሉ? ሲል ለተጠየቁት ጥያቄ በሰጡት ምላሽ እንደገለጹት፤ ቅሬታ የተነሳበትን ቦታ የማዕድን እና ኢነርጂ ቁጥር አራት ነዋሪዎች በግሪን ኤሪያ ሲጠቀሙበት መቆየታቸውን የሰሙት የማዕድን እና ኢነርጂ ቁጥር አራት ነዋሪዎች ለክፍለ ከተማ ቅሬታ ካቀረቡ በኋላ መሆኑን ይናገራሉ ።

ከነዋሪዎቹ ቅሬታ ጋር ተያይዞ ጉዳዩን ለማጣራት ከወረዳ 14 ጋር መነጋገራቸውን የገለጹት አቶ ጌታሁን ፤ ወረዳው ቦታው ባዶ ቦታ እንጂ ግሪን ኤሪያ አለመሆኑን ገልጸልኛል።

የማዕድን እና ኢነርጂ ቁጥር አራት ነዋሪዎች ቦታውን ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ በግሪን ኤሪያነት ሲጠቀሙት እንደቆዩ ይናገራሉ። ከዚህ ባለፈ በቦታው ላይ ውሃና መብራትም አስገብተውበታል። በአንጻሩ የእናንተ መስሪቤት ደግሞ ቅሬታ የተነሳበትን ቦታ በ2011 ዓ.ም ወደ መሬት ባንክ አስገብቶታል ። ይህ ሁለት ጉዳይ የሚቃረን ነገር ነው። እዚህ ላይ የእርስዎ አስተያየት ምንድን ነው? ሲል የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል የጠየቃቸው አቶ ጌታሁን ፤ የእርሳቸው መስሪያቤት ቦታውን ግሪን ኤርያ ብሎ የሚይዘው ቦታው ከፕላኑ አንጻር ግሪን ከሆነ እና የፕላን ጥበቃ ካለው ብቻ መሆኑን ይገልጻሉ።

ከዚህ ውጭ ግን ክፍት የሆኑ ቦታዎች በመረጃዎች መሰረት ይሰበሰቡና ወደ መሬት ባንክ ይገባሉ። ወደ ባንክ የገቡ ቦታዎችም ፕላኑ ከሚፈቅደው እና ከሚያዘው አንጻር ታይታ ለሚፈለገው የልማት ስራዎች እንዲውሉ ይደረጋል። የማዕድን እና ኢነርጂ ቦታውን በግሪን ኤርያነት ሲጠቀሙበት እንደቆዩ እና የማዕድን እና ኢነርጂ ቁጥር አራት ነዋሪዎች ቦታውን በአረንጓዴነት እያለሙ ስለመሆናቸውና በቦታው ላይ በጋራ ለመስራት የሚያስችሉ ደብዳቤዎችን ከቦሌ ክፍለ ከተማ የከተማ ውበት እና አረንጓዴ ልማት ቢሮ ጋር ለበርካታ ጊዜ መጻጻፋቸውን ሰነዶች ያሳያሉ። ስለዚህ ምን ይላሉ ? ተብለው የተጠየቁት አቶ ጌታሁን፤ ስለቦታው ከወረዳ 14 ለበርካታ ጊዜያት መጻጻፉቸውን ጠቁመው፤ ቅሬታ ያነሱት ሰዎች ቦታውም ለግሪን ኤርያ ሳይሆን ለመኪና ማቆሚያነት ይጠቀሙበት እንደነበርና ይህን ተከትሎ ቦታው ክፍት ቦታ ስለሆነ ወደ መሬት ባንክ ሊገባ መቻሉን ገልጸዋል።

የልማት ተነሽ የሆኑት አቶ ብርሃኑ የልማት ተነሺ ስለመሆናቸው በተለያዩ ደብዳቤዎች ተገልጿል። ከዚህ ጋር ተያይዞ በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 11 ቁጥር ቦ/ክ/ከ/ወ.11/4067/2013 በቀን 10/09/2013 ዓ.ም አርሶ አደሩ ለልማት ተነሽ መሆናቸው ለክፍለ ከተማው ጽፏል። በአንጻሩ ክፍለ ከተማው ደግሞ በቁጥር ቦ/ክ/ከ/የ/ይ/አስ/ጽ/ቤት 184996/2012 በቀን 1716/2012 ዓ.ም አርሶ አደሩ የልማት ተነሺ ስለመሆናቸው ከወረዳው ቀድሞ ጽፏል። መረጃ ከወረዳው ሳያገኝ ክፍለ ከተማው ከምን ተነስቶ ነው አርሶ አደሩ የልማት ተነሺ መሆናቸውን የጻፈው ? ሲል የአዲስ ዘመን ጋዜጣ አቶ ጌታሁንን ጠይቆ ነበር ።

ለተጠየቁት ጥያቄ ምላሽ የሰጡት አቶ አቶ ጌታሁን እንደተናገሩት፤ የአይሲቲ ፓርክ ተነሺዎች የተነሱት ለፕሮጀክት ስራ ነው ። ፕሮጀክት ሲሰራ ደግሞ የራሱ የሆነ አሰራር አለው ። በዚያ አሰራር መሰረትም ክፍለ ከተማው ደብዳቤ ከመጻፉ በፊት በወረዳ ደረጃ የልማት ተነሺ ስለመሆናቸው በቃለ ጉባኤ የተያዘ ሰነድ ነበር። ያ ሰነድ ከወረዳ ለክፍለ ከተማ ደርሶታል። ክፍለ ከተማም ያንን ሰነድ መሰረት አድርጎ መብት ለመፍጠር ደብዳቤ መጻፉን አመላክተዋል። የፕሮጀክት አሰራር ምን እንደሚመስል በግልጽና በዝርዝር አስረድተዋል። ዝግጅት ክፍሉም ከሚኖረው ሰዓት አንጻር ዝርዝር ጉዳዩን ትቶታል ።

የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍልም የአይሲቲ ተነሺ የሆኑ ሰዎችን ወረዳ 11 ድረስ በመሄድ ለማናገር ሞክሯል። እነኝህን ሰዎች አቶ ብርሃኑ መኮንን የተባሉት ግለሰብ የአይሲቲ ፕሮጀክት ተነሺ መሆናቸውን ታውቃላችሁ ? ሲል ነበር ጥያቄውን የጀመረው። ነዋሪዎችም አቶ ብርሃኑ መኮንን የተባሉትን ግለሰብ እንደማያውቋቸው ይናገራሉ። ስለዚህ ምን ይላሉ ስንል አቶ ጌታሁንን ጠይቀናቸው ነበር። ሰዎችን ሁሉንም አንድ ባንድ እከሌ እከሌ ተነሺ ነው ማለት እንደማይችሉ ገልጸው፤ ይህንን ጉዳይ በዝርዝር የሚያውቀው የወረዳ አስተዳደሩ መሆኑን ጠቁመዋል።

የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ወረዳ 11 ድረስ በአካል በመሄድ ለማጣራት እንደሞከረው ለአይሲቲ ተነሺዎች በ2014 ዓ.ም ካርታ የተሰራለት ሰው አለመኖሩን ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉ አካላት ይገልጻሉ። ስለዚህ እርስዎ ምን ይላሉ? ስንል ጠይቀናቸው ነበር ። አቶ ጌታሁንም መረጃው ውሸት እንደሆነና ከአይሲቲ ፕሮጀክት የተነሱ ሰዎች እስከዛሬዋ ቀን ድረስ መብት እየተፈጠረላቸው እንደሚገኙ ተናግረዋል።

አቶ ብርሃኑ መኮንን የተባሉት ግለሰብ አርሶ አደር ናቸው። በልማት የተወሰደባቸው መሬት ያለማ እና የእርሻ ስራ ይከወንበት የነበረ ነው። ምትክ የተሰጣቸው ቦታ ግን ገርጂ እየተባለ ከሚጠራው የከተማዋ ውድ ቦታ ላይ ነው። ስለዚህ ምን ይላሉ? ተብለው የተጠየቁት አቶ ጌታሁን እንደተናገሩት፤ ምትክ የሚሰጡት በመመሪያው መሰረት በቦሌ ክፍለ ከተማ ከሚገኝ ቦታ ነው። ይህን ተከትሎ የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል መመሪያው በምትክነት የሚሰጠው ቦታ ተመጣጣኝ መሆን እንዳለበት ይጠቁማል። ስለዚህ ከአይሲቲ ፓርክ አንስቶ ገርጂ ላይ መስጠት ተመጣጣኝ ነው ብለው ያስባሉ? ተብለው የተጠየቁት አቶ ጌታሁን «አዎ! ተመጣጣኝ ነው» የሚል ምላሽ ሰጥተዋል ።

የልማት ተነሺው 500 ካሬ ሜትር እንዲሰጠው ተወስኖለት ነበር እናንተ 400 ካሬ ሜትር ሰጣችሁ ? ሲል የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል አቶ ጌታሁንን ጠይቆ ነበር። አቶ ጌታሁንም ካለን የመሬት እጥረት አንጻር ታይቶ አንድ የልማት ተነሺ ፈቃደኛ እስከሆነ ድረስ 20 በመቶ ድረስ ተቀንሶ ሊሰጥ እንደሚችል በመመሪያ መቀመጡን ገልጸው ፤ አቶ ብርሃኑም በዚያ አግባብ መስተናገዳቸውን ይናገራሉ።

በርካታ የማዕድን እና ኢነርጂ ቁጥር አራት ነዋሪዎች ለተለያዩ ተግባራት የሚጠቀሙበትን የነበረን ቦታ በልማት ተነሺ ስም ለአንድ ሰው መሰጠቱ ተገቢ ነው ብላችሁ ታምናላችሁ ? ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ አቶ ጌታሁን ጥያቄው እንደማይመለከታቸው እና ጥያቄው የመልካም አስተዳደር ጉዳይ መሆኑን ጠቁመዋል።

የማዕድን እና ኢነርጂ ቁጥር አራት ነዋሪዎች አንድ መውጫ እና መግቢያ ብቻ ነው ያላቸው ። በደስታ እና በሃዘን የሚጠቀሙት ይሄንኑ ቦታ ብቻ ነው ። ይህ መሆኑን ማንም ሰው ከሰፈሩ ፕላን አይቶ የሚገነዘበው ነው። ከዚህ አንጻር የእናንተ መስሪያቤት ይህን ቦታ ለልማት ተነሺ መስጠቱ ተገቢ ነው ብለው ያምናሉ? ሲል ለተነሳው ጥያቄም ጉዳዩ የከተማ ፕላን ጽህፈት ቤት እንጂ እርሳቸውን እንደማይመለከት ተናግረዋል።

**ከቦሌ ክፍለ ከተማ መሬት ልማት እና አስተዳደር ጽህፈት ቤት የተገኙ የሰነድ ማስረጃዎች**

**ሰነድ አንድ**

በቀን 17/6/2012 ዓ.ም በቁጥር ቦ/ክ/ከ/የ/ይ/አስ/ጽ/ቤት 184996/2012 የቦሌ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ አስተዳደር ጽህፈት ቤት የመደበኛ ይዞታዎች ካርታ ዝግጅት የስራ ሂደት ለመሬት ልማትና ከተማ ማደስ ጽህፈት ቤት የሚከተለውን ደብዳቤ ጽፎ ነበር ።

በአይሲቲ ፕሮጀክት ተነሺ የሆኑ ባለይዞታዎችን በተመለከተ በዴስኩ በኩል የተሰጠ ውሳኔ ሃሳብን ስለማሳወቅ መሆኑ በጉዳዩ ተመላክቷል።

የቦሌ ክፍለ ከተማ የመደበኛ ይዞታዎች ካርታ የስራ ሂደት አግባብ ያለው አካል ሳይፈቅድ የተያዙ ቦታዎችን ለማስተካከል እና ለመከላከል ባወጣው የመመሪያ ቁጥር 18/2006 መሰረት በልማት ተነሺ የሆኑ ባለይዞታዎችን

30/09/13

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
የቦሌ ክፍለ ከተማ
የመሬት ልማትና ከተማ ማደስ ጽ/ቤት

Addis Ababa City Administration
Bole Sub City
Land Development, and Urban
Renewal Office

ቀን፡-17/09/13
ቁጥር፡- ቦ/ክ/ከ/መ/ል/ከ/ማ/ጽ/2285/13

**በቦሌ ክ/ከተማ መሬት ልማትና ከተማ ማደስ ጽ/ቤት**

**ለለማ መሬት ዝግጅት ዋና የስራ ሂደት**

**አዲስ አበባ**

**ጉዳዩ፡- የምትክ ቦታ ማስተላለፍን ይመለከታል።**

ከታች ስማቸው የተገለፁት ግለሰብ በወረዳ 11ክልል ውስጥ ICT ፓርክ ፕሮጀክት ምክንያት ሙሉ ተነሺ ሲሆኑ በመመሪያው መሰረት የይዞታ አስተዳደር የሽ/ጊ/አገ/ፐ/ጽ/ቤት መብት በፈጠረላቸው አግባብ ለተነሺው የሚገባቸውን የምትክ ቦታ ስፋት በመመሪያ ቁጥር19/2006 መሰረት የተወሰነላቸው ስለሆነ ምትክ ቦታውን አዘጋጅታችሁ በመሬት ባንክና ማ/ጽ/ቤት በኩል እጣ በማስወጣት እንድታስተላልፉላቸው ማህደሩን ከዚህ ሸኚ ደብዳቤ ጋር ስንልክ በቀጣይ የሚነሱትን ቦታ ለማፅዳት ቦታውን እንደተረከቡ በግልፅ እንድታሳውቁን የተለመደ የስራ ትብብራችሁን እንጠይቃለን።

| ተ.ቁ | ስም ዝርዝር | የቦታ ስፋት በካሬ ሜትር | የፕሮጀክቱ ስም | የቦታው አገልግሎት | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ተስፋዬ መኮንን ደገፋ | -500- | ICT ፓርክ | መኖሪያ | |
| 2 | ኬኔ መኮንን ደገፋ | -500- | ICT ፓርክ | መኖሪያ | |
| 3 | ብረሃኑ መኮንን ደገፋ | -500- | ICT ፓርክ | መኖሪያ | |
| 4 | ፋንቱ መኮንን ደገፋ | -500- | ICT ፓርክ | መኖሪያ | |
| 5 | ጫላ መኮንን ደገፋ | -500- | ICT ፓርክ | መኖሪያ | |
| 6 | ቤኛ መኮንን ደገፋ | -500- | ICT ፓርክ | መኖሪያ | |
| 7 | የሮስን መኮንን ደገፋ | -500- | ICT ፓርክ | መኖሪያ | |
| 8 | እፍቱ መኮንን ደገፋ | -500- | ICT ፓርክ | መኖሪያ | |

ከሰላምታ ጋር
ጌታሁን ነጋሳ
የወሰን ማስከበር ዋና የስራ ሂደት

**ግልባጭ፡-**
**በቦሌ ክ/ከተማ አስተዳደር**

- ለመሬት ልማትና ከተማ ማደስ ጽ/ቤት
- ለወሰን ማስከበር ዋና የስራ ሂደት
- ለካሳ ግምትና ምትክ ኦፊሰር
- ለማህደሩ

አዲስ አበባ

251-011-862413 ✉ 26920 Fax +251-011-663 28 36 መልስ ሲጽፉልን የደብዳቤውን ቀንና ቁጥር ይግለፁ!

መስተንግዶ እንድንሰጥ በቁጥር አአ/መልማቢ/01/1710 በቀን 10/10/06 እና ይአስ /848/07 በቀን 27/01/2007 ዓ.ም ተገልጻል። ከዚህ ባሻገር የመሬት ልማት እና ማኔጅመንት ቢሮ ስለ አርሶ አደር እና የአርሶ አደር ልጆችን መስተንግዶ አሰጣጥ በቀን 15/6/08 በቁጥር አአ/መልማቢ/ 01/2245/08 እና በቀን 11/8/10 በቁጥር ይአስ/2235/10 የካቢኔ የውሳኔ አቅጣጫ ተቀምጧል።

በመሆኑም በመመሪያው በአንቀጽ 6 በንዑስ አንቀጽ 6 ነጥብ 4 ከሚያዚያ 1997 ዓ.ም የተያዙ ስለመሆናቸው ቢረጋገጥም የከተማ ፕላን እና አካባቢ ሽንሻኖ የማይቀበላቸው ህጋዊ ባልሆነ መንገድ የተያዙ ይዞታዎች ተጣርቶ በሚቀርበው መረጃ መሰረት የግለሰቦችን ስም በማደራጀት በደንቡ ላይ በተደነገገው መሰረት ምትክ ቦታ እንዲያገኙ ለመሬት ልማት እና ከተማ ማደስ ጽህፈት ቤት እንዲተላለፍ በሚል ተገልጿል።

ይህን መነሻ በማድረግ በአይሲቲ ፓርክ ልማት ተነሺ ሆነው ከመሬት ልማትና ከተማ ማደስ ጽህፈት ቤት መረጃቸው ተደራጅቶ ዝርዝራቸው ከተላኩት የልማት ተነሺዎች መካከል በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 የማዕድን እና ኢነርጂ ቁጥር አራት የአረንጓዴ ስፍራ ወይም ግሪን ኤርያን በልማት ተነሽነት ስም የተሰጡት አቶ ብርሃኑ መኮነን አንዱ መሆናቸው ተመላክቷል። በዚህ መሰረትም አቶ ብርሃኑ መኮነን እና ቤተሰባቸው ለእያንዳንዳቸው 500 ካሬ ሜትር መሰጠት እንዳለባቸው ተገልጿል።

**ሰነድ ሁለት :-**

በቦሌ ክፍለ ከተማ የወረዳ 11 ዋና ስራ አስፈጻሚ ለቦሌ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ከተማ ማደስ ጽህፈት ቤት በቁጥር ቦ/ክ/ከ/ወ/11/4067/2013 በቀን 10/09/2013 ዓ.ም የተጻፈ ደብዳቤ እንደሚጠቁመው የደብዳቤው ዓብይ ጉዳይ መረጃ መላክን የሚመለከት መሆኑን ገልጾ፤ በዚህም ደብዳቤ ወረዳው ከዚህ ቀደም በቁጥር ቦ/ክ/ከ/ወ.11/ጽ/ቤት 3924/2013 በቀን 01/07/2013 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ 165 አርሶደሮች እና አርሶ አደር ልጆች በአይሲቲ ፓርክ ልማት ተነሺ መሆናቸውን አጣርቶ መላኩን እና የቀሩትንም «የኤክስ ዋይ ኮርድኔት » አጣርቶ እስከሚልክ ድረስ የተላኩት የ165 አርሶ አደር ፋይሎች እንዲስተናገዱ እና አስፈላጊውን ትብብር እንዲደረግላቸው የሚገልጽ ሲሆን ከ165ቱ አርሶ አደሮች መካከልም አቶ ብርሃኑ መኮንን እና ቤተሰቦቻቸው እንደተካተቱ ተመላክቷል።

**የጋዜጠኛው ትዝብት**

**ትዝብት አንድ ፡-** ውዝግብ የተነሳበትን ቦታ በአካል ተገኝቼ ተመልክቻለሁ። ግሪን ኤርያው ውስጥ ቆርቆሮ በቆርቆሮ የተሰሩ ውሃ እና መብራት የገባባቸው ቤቶች አሉ። የአካባቢው ማህበረሰብም ተቀያሪ መውጫ እና መግቢያ ስሌለለው ግሪን ኤርያውን ከግሪን ኤርያነት ባለፈ በደስታ እና በሃዘን ጊዜ ድንኳን በመትከል ጉዳያቸውን ሲከውኑ ተመልክቻለሁ። ይህ ቦታ ባይኖር ኖሮ አንድ መውጫ እና መግቢያ ያለው ይህ ማህበረሰብ በሃዘን እና በደስታ መውጫ እና መግቢያ ማግኘት እንደማይችልና ማናቸውም አይነት እንቅስቃሴ ለማድረግ እንደሚቸገር ለመታዘብ ችያለሁ።

**ትዝብት ሁለት ፡-** የልማት ተነሺ የተባሉትን ግለሰብ በአካል ማግኘት ስላልቻልን የልማት ተነሺ ናቸው የተባሉትን ግለሰብ ለማግኘት በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 11 ድረስ በመገኘት የአይሲቲ የልማት ተነሺ የነበሩ ሁለት ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉ ሰዎች አቶ ብርሃኑ መኮነን ያውቁ እንደሆን ለመጠየቅ ሞክረን ነበር። ነገር ግን የተባሉትን ግለሰብ በአይሲቲ ፕሮጀክት መነሳታቸውን እንደማያውቁ እና ሰውየውንም ፈጽሞ እንደማያውቋቸው ነግረውናል።

**ከአዘጋጁ፤** ተነሺ አርሶ አደር ናቸው የተባሉትን አቶ ብርሀኑ መኮነን ለማግኘት ጥረት አድርገናል። የልማት ተነሺ ናቸው የተባሉ ሰዎችንም አግኝተን ጭምር ለማነጋገር ሞክረናል፤ ሆኖም ግን እናውቃቸዋለን የሚል አካል ማግኘት አልቻልንም። እርሳቸውን በአካል ወይም ተንቀሳቃሽ ስልካቸውን ማግኘትም አዳጋች ሆኗል። እኚህ የልማት ተነሺ የተባሉትን ግለሰብ ካሉ ልናነጋግራቸው ሀሳባቸውንም ልናደምጥ ዝግጁ ነን። ሌሎች በዚህ ዙሪያ ሀሳብ፣ መረጃ፣ አስተያየት ለመስጠት ለሚፈልጉ ሁሉ ዝግጅት ክፍላችን የሚያስተናግድ መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፣ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

## "ምን ሠርተን እንለፍ?"

**በኩረ ቃል፤**

የጽሑፌን ዋና ርዕስ የተዋስኩት ከረጂም ዓመታት ወዳጄ ከመምህርና ደራሲ ስሜ ታደሰ የመጽሐፍ ርዕስ ነው። መምህር ስሜ ታደሰ በሚወደው የመምህርነት ሥራ ላይ እንደተጋና ሙያውን እንዳደነቀ እነሆ ድፍን አርባ ዓመትን አስቆጥሯል። ዛሬም ከዚሁ ተከባሪ ሙያው ላይ ሳይለይ ትውልድን በመቅረጽ ላይ ይገኛል።

መምህር ስሜ ታደሰ ከዋነኛው የማስተማሩ ሥራ ጎን ለጎን አሥር ያህል ዳጎስ ያሉ የጥናት፣ የምርምርና በማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ መጻሕፍትን ለአንባቢያን በማድረስ ረገድም አንቱታን አትርፏል። ይህ ዕንቁ መምህር "ያልተዘመረላቸው" ከሚባሉ የአገር ባለውለታ ዜጎች ዝርዝር ውስጥ ቢካተት ተገቢም አግባብም እንደሆነ የዚህ ጸሐፊ እምነት ነው።

ይህ መምህርና ደራሲ ሁለት አሥርት ለሚጠጉ ዓመታት እያስተማረበት ባለው ኢንተርናሽናል ት/ቤት ውስጥ በተለየ ሁኔታ እያከናወነ ያለው የአርአያነት ተግባርና አግልግሎቱ ለሙያውና ለሕይወት ያለውን ጥርት ያለ ተልእኮና አክብሮት በሚገባ የሚያመለክት ነው። ካስተማራቸውና እያስተማራቸው ካሉት ተማሪዎቹ መካከል አንዳንዶቹ የቁንጮዎቹ የአገር መሪ ልጆች ሲሆኑ ብዙዎቹም የከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች፣ የታዋቂ ዜጎች፣ በተሰማሩበት የንግድ ሥራቸው ወይንም የተለያዩ የሙያ ዘርፎች አንቱታን የተጎናጸፉ ወላጆች ያፈሯው ልጆች ናቸው።

መምህሩ የሙያ ግዴታውን እየተወጣ ያለውም በክፍል ውስጥ ወስኖ ለሚያስተምራቸው ተማሪዎቹ ብቻ ሳይሆን ለወላጆቻቸው ጭምር የጻፋቸውን መጻሕፍት በአደራ እየላከ በየቤታቸው ከልጆቻቸው ጋር እንዲወያዩባቸውና እንዲሟገቱባቸው በማድረግ ረገድም ፈር ቀዳጅነቱን በሚገባ እያስመሰከረ መሆኑ ለየት ያደርገዋል።

ከጻፋቸው መጻሕፍት መካከልም በተለይም ይህ ጽሑፍ በርዕስነት የተዋሰው "ምን ሠርተን እንለፍ?"፣ "ተሳስቼ ነበር" በሚል ርዕስ በሁለት ተከታታይ ቅጾች፣ "የተከዳው እውነት" እና "ለእውነት እንቁም" የሚሉት አምስት መጻፍሕት በተለየ ሁኔታ በርዕሳቸውም ሆነ በይዘታቸው በሰፊ አንባቢያን ዘንድ በተማሪዎቹና በወላጆቻቸው መካከል ጥሩ የመወያያና የመከራከሪያ ርዕሰ ጉዳዮች እንደሆኑ ለማረጋገጥ ተችሏል።

መምህር ስሜ በአንድ ወቅት በማስተማር ተግባሩ ላይ እያለ በድንገተኛ ሕመም ተዝለፍልፎ በመውደቁ የትምህርት ቤቱ የሥራ መሪዎች ወደ ተለያዩ የሕክምና ተቋማት አስቸኳይ እርዳታ እንዲያገኝ ቢወስዱትም የጤና ባለሙያዎቹ "በተለይም በሁለቱ ተቋማት" የሰጡት መልስ "ልንረዳው አንችልም" የሚል ተስፋ አስቆራጭ ነበር።

በአጋጣሚ ለሦስተኛ ጊዜ በተገኘበት የሕክምና ተቋም ውስጥ ታናሽ እህቱ በጤና ባለሙያነት ትሠራ ስለነበር ወደ ሞት እየተቃረበ የነበረው ወንድሟ ሳታስበው እጇ ላይ በመውደቁ ኡኡታዋን በማቅለጧ እንደ መባነን ብሎ ነፍስ የዘራው መምህር ወዲያው የታወሰው ህልፈተ ሕይወቱ ሳይሆን "ምን ሠርቼ ነው የማልፈው?" የሚለው መሠረታዊ ጥያቄ እንደነበር ደጋግሞ በመጻሕፍቱ ውስጥ ጠቅሶታል። ከበሽታው እንዳገገመም ሳይውል ሳያድር ይኼንኑ ሃሳብ የሚወክል ርዕስ የሰጠውን መጽሐፍ ለንባብ አብቅቷል።

ይህ ዐምደኛ የዚህን አርአያ ሰብ መምህርና ደራሲ ገጠመኝ ዘርዘር አድርጎ ለማስታወስ የገፈፋውና እረፍት

| ዜና መዋዕላችን | የዓመታት ስሌት | የመቶኛ ስሌት |
|---|---|---|
| በማንቀላፋት | 23 ዓመታት | 32.9% |
| በሥራ | 16 ዓመታት | 22.8% |
| የሚዲያ ፍጆታ | 8 ዓመታት | 11.4% |
| በመመገብ | 6 ዓመታት | 8.6% |
| በመጓዝ | 6 ዓመታት | 8.6% |
| በመዝናናት | 4.5 ዓመታት | 6.4% |
| በህመም | 4 ዓመታት | 5.8% |
| በመልበስ/በመዋብ | 2 ዓመታት | 2.8% |
| ሥርዓተ ሃይማኖት | 0.5 ዓመታት | 0.7% |
| ድምር | 70 ዓመታት | 100% |

የነሳው የአገሩ ወቅታዊ ጉዳይ ነው። ብዙው "ነፍስ አወቅ" ኢትዮጵያዊ ዜጋ በየተግባሩና በየውሎ መስኩ ልክ እንደ ወዳጄ የመጽሐፍ ርዕስ "ምን ሠርቼ ልለፍ? ለእውነት እቆማለሁ እና ተሳስቼ ነበር!" ብሎ ቢጠይቅና መልሱን ለማግኘት ቢሞክር ኖሮ የአሳረኛዋን አገራችንን መልክ ያጠየመውና ያጎሳቆለው የዛሬው መከራችን አንድም ባልበረታብን አለያም ዕድሜው ባጠረ ነበር።

ይህ ምኞታችን ተግባራዊ ባይሆን እንኳን "ልጄ ሆይ እንደምትሞት ሆነህ ኑር፤ እንደምትኖር ሆነህ ሥራ" የሚለው የአዛውንቶች እድሜ ጠገብ ምክር የእያንዳንዱ ዜጋ የሕይወት መርህ ሆኖ ዕንቆቅልሻችንን እያወሳሰበ ካለው ግርግርና ቱማታ መስከንና መረጋጋት በቻልንም ነበር። በፈጣሪ እስትንፋስ ተፈጥሯል የሚባለውና የኅሊና ባለንብረት የሆነው የሰው ልጅ ያለ በቂ ምክንያት የንጹሐንን ደም አፍስሶ እንደምን የሰላም እንቅልፍ አግኝቶ ተኝቶ ያድራል? በዛሬዋ ጀንበር እያጋጠምን ያለው አንዱ የመከራችን ዕንቆቅልሻችን ይህ ነው።

አገርና ሕዝብን ከጥፋትና ከወድመት ከመታደግ ይልቅ የከፋት ዘዴዎችን ሲያውጠነጥኑ ማደርንስ በምን ቋንቋ መግለጽ ይቻላል? አየራችንን የበከሉት እኒህን መሰል ይዘት ያላቸው ዜናዎች እንዴት እየተስፋፉ "የባህል ያህል" ሥር ወደ መስደድ ደረጃ ሊደርሱ እንደቻሉ ቆም ብለንና ጨክነን ልንወያይባቸውና ልንመክርባቸው ይገባል።

የፖለቲካውን ጡዘት በሴራ አክርሮ ሕዝብ እንዳይረጋጋ ማድረግ፣ የኢኮኖሚውን አውታር በማናጋት ዜጎች ቀለባቸው እምባ እንዲሆን በስግብግብነት ተጠፍሮ በጭካኔ የዕለት እንጀራ ላይ መፍረድ፣ ፍትሕን ማጣመም፣ ተገልጋይን ማስለቀስ፣ በማንነት ፍረጃ ላይ እየተረባረቡ ከሰብእና ማነስ ወዘተ. ትሩፋቱ ምን ሊሆን እንደሚችል ማሰቡ በራሱ ናላን ያዞራል። እነዚህን መሰል ማሕበራዊ ጉድፎች መቅረፍና ማስወገድ የሚቻለው ከከዳነው እውነትና ከኅሊናችን ጋር እርቅ ፈጥረን ለራሳችንና ለሌሎች የሰላም መልእክተኛ ሆነን ስንገኝ ብቻ ነው።

**ለራስ የሚታወጅ —የክተት ጥሪ"፤**

በዚህ ዕድሜ ጠገብ ጋዜጣ ላይ እጅግ በርካታ አገራዊ ህፀፆችን እየነቀስንና መልካሙን እያበረታታን ያለ መታከትና ያለ መቆጠብ መጻፍ ከጀመርን እነሆ ወደ አራት አስርት ዓመታት ልንጠጋ ጫፉ ላይ ደርሰናል። በመቶዎች ምናልባትም በሺህዎች ሊቆጠሩ የሚችሉት አብዛኞቹ ጽሑፎች በአገራዊ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩና ወደ ኅሊናችንና ወደ ቀልባችን ተመልሰን እንድንሰክን የሚያበረታቱ ናቸው።

በአንድ ወቅት ለንባብ የበቃን አንድ የምርምርና የጥናት ውጤት መነሻ በማድረግ ይሄው ጸሐፊ በአንድ አገራዊ መጽሔት ላይ ሃሳቡን ለማጋራት ሞክሯል። ጽሑፉ ለንባብ ከበቃ በኋላ በርካታ አስተያየቶች ደርሰውት እንደነበርም ያስታውሳል። ብዙ አንባቢያን በትንታኔው መደሰታቸውንና የተዘረዘረው እውነታ እንዳባነናቸው ቢገልጹም ጥቂት የማይባሉ አንባቢያን ግን በግኝቱ ላይ ልዩ ልዩ ጥያቄዎችን ማንሳታቸው አልቀረም ነበር።

ጥናቱ በተለያዩ አገራት ውስጥ የተሰራ ሲሆን መነሻ የተደረገውም በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ (መዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ 90 ቁጥር 10) የተጠቀሰውና በብዙዎች ዘንድ እንደ ብሂል ተደጋግሞ የሚነገረውና የሰው የዕድሜ ጣሪያ የተወሰነበትን "የዘመኖቻችን ዕድሜ ሰባ ዓመት ቢበረታ ሰማንያ ዓመት ነው። ቢበዛ ግን ድካምና መከራ ነው" የሚለው ሃሳብ ነው። በጥናቱ ላይ የተሳፉት የተለያዩ የጥናት ዘርፍ ምሁራን በጋራ ተስማምተው የወሰኑትም "ሰባ ዓመት" የሚለውን ጣሪያ ሲሆን ይህቺን ቁራጭ አማካይ ዕድሜ በምንና ምን ጉዳዮች ላይ ሸንሽነን በማዋል ኖረን እንደምናልፍ በሚገባ በሰንጠረዥ አመላክተዋል።

ከእነ ጥያቄያችንም ቢሆን በአጥኚዎቹ የተዘጋጀውን የስታስቲክሱን መረጃ እንደ መነሻ በመውሰድ የራሳችንን አስተያየት እያከልንበት ማንነታችንን እንድንፈትሽበት ትንታኔውን እንደሚከተለው እናስታውሳለን።

ይህ የጥናት ግኝት ከአገር አገር፣ ከባህል ባህል፣ ከተሞክሮ ተሞክሮ ወዘተ. ሊለያይ እንደሚችል በሚገባ ይታወቃል። የእያንዳንዱ ሰው የሕይወት ተሞክሮና አኗኗርም በሸንሻኖ ከቀረበው ዜና መዋዕል ጋር በእጅጉ ሊጻረርም ሆነ ሊደጋገፍ እንደሚችል ለማናችንም አይጠፋንም። የቁጥሩና የመቶኛው ስሌት ይለያይ ካልሆነ በስተቀር ከእውነታው ነፃ መሆን ግን ከቶውንም እንደማይቻል ማሳወቁ አይከፋም።

ሌሎችን ዝርዝር ጉዳዮች ለጊዜው እናቆይና እያንዳንዱ አቅሙ ለሥራና ለኃላፊነት፤ ጤንነቱም አስተማማኝ የሆነ ግለሰብ በዕድሜ ቆይታ ዘመኑ በተግባሩ ላይ የሚያሳልፋቸው አሥራ ስድስት ዓመታት (22.8%) እንዳሉ ሆነው፤ ስሌቱ ሊበዛም ሆነ ሊያንስ እንደሚችል ልብ ይሏል፤ ጥያቄው መሆን የሚገባው "ስንት ዓመት በሥራ ላይ ተጠምጄ ኖርኩ?" ማለት ብቻም ሳይሆን "የማልፈው ምን ቋሚ ሐውልት አቁሜ ነው?" የሚለው ሊሆን ይገባል።

ከአሁን ቀደም በዚሁ ጋዜጣ ላይ Todd Henry የተባሉ እንግሊዛዊ ደራሲ "Die Empty" በሚል ርዕስ የጻፉትን እጅግ ተወዳጅና ተነባቢ መጽሐፍ አስመልክቼ ዘርዘር ያሉ ሃሳቦችን ማካፈሌ አይዘነጋም። የመጽሐፉ ዋነኛ የጭብጥ አስኳል፤ "በተሠጠህ የሕይወት ዘመን ያለኽን እውቀት፣ ሀብት፣ ብቃትና በጎነት፣ ያለ ስስት ለሰው ልጆች ሁሉ የጋራ በረከት እንዲሆን አንጠፍጥፈህ እለፍ እንጂ ለአፈር ቀለብ እንዲሆን በክፋትና በስግብግብነት ተገንዘህ ዓለምን አትሰናበት" የሚል እንደነበር የጋዜጣው ቤተሰቦች ያስታውሱ ይመስለናል።

የመምህርና ደራሲ ስሜ ታደሰን "ምን ሠርተን እንለፍ?" የመጽሐፍ ርዕስም ለመዋስ ያስፈለገበት ዋነኛ ምክንያት ይኸው ነው። ርዕሱ ይኽንን መሰል ሞጋች እውነታ በሚገባ ማጉላት ብቻም ሳይሆን ለዛሬው ዕለተ ረቡዕ የቀረበውን የመልእክታችንን አንኳር ሃሳብ የመሸከም አቅሙም ከፍ ያለ መሆኑን በማስታወስ ጭምር።

በየትኛውም አገርና ባህል ወይንም ዐውድ ውስጥ የተፈጠረ የሰው ልጅ በሙሉ (ሰባም ይሁን ሰማንያ ወይንም መቶ ከምናምን) የተቆረጠለት ዕድሜው አብቅቶ ግባ መሬቱ እንደሚፈጸም ይዘነጋ ካልሆነ በስተቀር ሊረሳ የሚችል አይደለም። ትኩረት ሊሰጥበት የሚገባው ዋነኛው ሃሳብ የአሟሟታችን ዓይነትና የሞታችን ጉዳይ ብቻ ሳይሆን "ምን ሠርተን እንለፍ?" የሚለው ሞጋች ጥያቄ ቀዳሚ ትኩረታችን ሊሆን ይገባል። ይህንን የማንፈጽም ከሆነ ግን "ሞት ሲደርስ ቄስ፤ ጦር ሲደርስ ፈረስ" ይሆንና በፀፀት እየተቀጣን ወደ መቃብራችን ለማዝገም እንገደዳለን።

እያንዳንዱ ነፍስ አወቅ ዜጋ ይህንኑ እውነታ ተረድቶ የበጎነቱን አሻራ ዘር ያለንፍገት በመዝራት የኢትዮጵያና የኢትዮጵያዊነት መልክና የአኗኗራችን ውበት እንዲደመቅ የራሱን ጠጠር አኑሮ ቢያልፍ አገራችንና ሕዝባችን እንደምን ከፍ ወዳለ ደረጃ መመንደግ እንደሚችሉ ለመገመት አይከብድም።

**"ምን ሠርቼ ልለፍ፤ የጧት ገድ ይሁን፣**
**ማምሻ ላይ ትካዜ፤ መርዶ እንዳይሆንብን።**

አለች ይባላል ሙሾ አሙሺዋ አስረጋጅ። ይኼው ነው። ሰላም ይሁን።

# በመሰረታዊ የምግብ ምርቶች ላይ የሚታየውን ክፍተት መሙላትን ያለመው ጥናት

**ፍሬሕይወት አወቀ**



አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ የአፍሪካ ህብረትና የዓለም አቀፍ ተቋማት መቀመጫ እንደመሆኗ በፖለቲካ፣ በማህበራዊና በኢኮኖሚ እንቅስቃሴዋ ከክልል ከተሞች በተለየ ሁኔታ ሞቅና ደመቅ ትላለች። በመሰረተ ልማቶቿም የተሻለችና ለኑሮ ምቹ የሆነች ከተማ ናት።

ለኑሮ ምቹ ሁኔታዎች ያሏት፣ በርካታ የአገሪቱ ዜጎች ስራ ፍለጋ፣ ሌሎች ደግሞ በከተማዋ ካለው አንጻራዊ ሰላም ጋር በተያያዘ የዜጎች ምርጫ እየሆነች የምትገኘው ይህች መዲና፣ በሰላም አጦትና በመሳሰለው የተቸገሩ የጎረቤት አልፎም ተርፎ የሩቅ አገሮች ስደተኞች ምርጫም ሆናለች። ከተማዋ የእነዚህን ሁሉ ዜጎች መሰረታዊ ፍላጎቶች ለመመለስ እየተውተረተረች ትገኛለች።

የብዙሃኑ መኖሪያ የሆነችው አዲስ አበባ አሁን አሁን ግን በኑሮ ውድነት ያዳከማት ትመስላለች። በአራቱም አቅጣጫ በየጊዜው እየፈለሰ ወደ ጉያዋ ለሚተመው ህዝብ መሰረታዊ ፍላጎቱን ልታሟላለት አቅም አጥታለች። የመኖሪያ ቤት አቅርቦት፣ የጤና፣ ንጹህ የመጠጥ ውሃ፣ የትምህርትና ሌሎች ማህበራዊ ማዳረስ ፈተና ሆኖባታል። ከሁሉም በላይ መቆሚያ ባልተገኘለት የኑሮ ውድነት በእጅጉ እየተፈተነች ትገኛለች።

ከተማዋ የኑሮ ውድነቱን ለማርገብ የተለያዩ ተግባሮችን ስታከናውን ቆይታለች። መሰረታዊ የምግብ ሸቀጦችን በሸማቾች ማህበራት በኩል ለህዝቡ ለማቅረብ በትኩረት መስራቷን ቀጥላለች። ህገወጦችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር እየሰራ ይገኛል። በአቅርቦትና ፍላጎት መካከል ያለውን ክፍተት ለመሙላት የከተማዋ አስተዳደር የፋይናንስ አቅርቦት በማድረግ ጭምር እየሰራ ነው። የህብረት ስራ ማህበራት ከከተማ አስተዳደሩ ጋር እየሰሩ ናቸው።

ችግሩ እየተቃለለ ይመጣል ሲባል እየተባባሰ መጥቷል። የሸቀጦች የዋጋ ንረት ህዝቡን ሰቅዞ የያዘው ቀዳሚ ችግር ነው። ማህበረሰቡ እየተፈተነበት ያለው የኑሮ ውድነት በእጅጉ እያሳሰበው መምጣቱን የሚገልጸው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ፣ በጥናት ላይ ተመስርቶ መፍትሔውን ለማፈላለግ እየሰራ መሆኑን ይገልጻል።

ቢሮው ሰሞኑን ባዘጋጀው መድረክ በአዲስ አበባ ከተማ የኑሮ ውድነት እየከፋ ሊመጣ የቻለው በተለያዩ ምክንያቶች መሆኑን በጥናት ማረጋገጡን የከተማ አስተዳደሩ አስታውቋል። በተለይም በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ከተማዋ የሚፈልሰው የህዝብ ቁጥር በየጊዜው እየጨመረ መምጣቱ በመሰረታዊ የምግብ ሸቀጣ ሸቀጦች ዋጋ ላይ ከፍተኛ ንረት እያስከተለ መሆኑንም በጥናቱ ማረጋገጥ እንደተቻለ አመላክቷል።

የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ በከተማው የሚስተዋለውን የንግድ እንቅስቃሴ ጤናማ ለማድረግና የዋጋ ግሽበትን ለመከላከል የተለያዩ ዘዴዎች ቀይሶ እየሰራ መሆኑን የጠቀሱት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ ኃላፊ አቶ አደም ኑሪ፤ የኑሮ ውድነቱን መነሻ በማድረግ በመሰረታዊ የምግብ ፍጆታ ምርትና አቅርቦት ላይ ለሚስተዋለው ችግር መፍትሔ ለመስጠት ጥናቱ መደረጉን አስታውቀዋል።

በጥናቱም የተለያዩ አካላት ተሳትፎ ያደረጉ ሲሆን፤ የጥናቱ ውጤትም የምግብ ሸቀጦችን የዋጋ ንረት ገታ ለማድረግ የሚያስችል እንደሆነ በመድረኩ ተጠቁሟል።

አቶ አደም እንዳብራሩት፤ ቢሮው ተነሳሽነቱን ወስዶ ከተለያዩ አካላት ጋር ባደረገው ጥናት የተገኘው ውጤት አዲስ አበባ ከተማ በተለያዩ ምክንያቶች ለከፍተኛ የምግብ ዋጋ ንረት ተጋላጭ መሆኗን ማረጋገጥ አስችሏል። ከተማ አስተዳደሩም የምግብ ዋጋ ንረትን ተከትሎ የሚመጣውን የኑሮ ውድነት ለማረጋጋት በጊዜያዊነትና በዘላቂነት መፍትሔ ያመጣሉ ያላቸውን የተለያዩ አማራጮችን ወስዶ እየሠራ ነው።

የገበያ ማዕከላትን በመገንባትና በማስፋፋት፣ የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶች አቅርቦትን ማሻሻል፣ የመሰረታዊ ፍጆታ ምርቶች በፍትሃዊነት ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ፣ በንግድ ስርዓቱ ላይ ቁጥጥር በማካሄድ የዋጋ ንረትንና የምርት ቅሸባን መከላከል ላይ እየተሰራ መሆኑን ጠቅሰው፣ የገበያ መሰረተ ልማትን በማስፋፋት ዘመናዊ ቴክኖሎጂን ሥራ ላይ በማዋል፣ በከተማው ህገወጥና የኮንትሮባንድ ንግድን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በከተማው ፍትሃዊ፣ ዘመናዊና በውድድር ላይ የተመሰረተ የንግድ ሥርዓት ለማስፈን ከፍተኛ ርብርብ እየተደረገ እንደሚገኝ ኃላፊው አብራርተዋል።

በመሰረታዊ የፍጆታ ምርት አቅርቦትና ፍላጎት ላይ የሚታየውን ክፍተት ለመሙላት የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ ጥናቱን መሰረት በማድረግ እንደሚሰራም ተጠቁሟል። ጥናቱ ለመሠረታዊ የምግብ ሸቀጦች ዋጋ ንረት ትልቁ መንስኤ የአቅርቦትና የፍላጎት አለመመጣጠን መሆኑን ማመልከቱን አቶ አደም ተናግረዋል። በተመሳሳይ መልኩ የንግድ ሥርዓቱ ክትትልና ቁጥጥር መላላት፣ ምርትን የመደበቅ እና በግብይት ሰንሰለቱ የበርካታ ተዋናዮች ጣልቃገብነት እንዲሁም የጸጥታ ችግር ለዋጋ ንረቱ ሌላኛዎቹ ምክንያቶች መሆናቸውን በጥናቱ መለየት እንደተቻለ ነው ያስረዱት።

የጥናቱ ቡድን መሪ አቶ እንዳለ ተገኝ እንዳብራሩት፤ የጥናቱ ዋና ዓላማ የአዲስ አበባ ከተማ መሰረታዊ የምግብ ሸቀጦች አቅርቦትና ፍላጎት አለመጣጣም ላይ የሚታዩ ክፍተቶችን መሙላት፣ የመፍትሔ አመላካቾችን ማቅረብም ነው። ጥናቱ በመሰረታዊ የምግብ ሸቀጦች ላይ እየተስተዋለ ለሚገኘው የዋጋ ንረት ከመላ ምት ያለፈ ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት ያስችላል።

አምስት ዓላማዎችን ይዞ ጥናቱ መካሄዱን ጠቅሰው፣ በቀዳሚነት መሰረታዊ የምግብ ምርቶች በጥናት መለያታቸውን፤ ፍላጎቱ ምን ይመስላል፣ አቅርቦቱስ ምን ያህል ነው፣ ክፍተቱ በምን ሁኔታ ላይ ነው የሚሉትን መመለስ የቻለ ጥናት እንደሆነም አስታውቀዋል፤ የከተማዋ የምግብ ምርት አቅራቢ ቦታዎችንም መለየት እንደሚያስችል አብራርተዋል።

እንደ አቶ እንዳለ ገለጻ፤ በመዲናዋ የሚዘወተሩት የምግብ ምርት አይነቶች 23 መሆናቸውን በጥናቱ መለየት ተችሏል፤ እነዚህም ጥራጥሬ፣ አትክልትና ፍራፍሬ፣ የእንስሳት ተዋጽኦ እና የኢንዱስትሪ ምርቶች በሚል ይመደባሉ። በጥናቱ መሠረት፣ በአሁኑ ጊዜ የመዲናዋ ሕዝብ ብዛት አምስት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ደርሷል፤ ከሕዝቡ አጠቃላይ ወጪ 52 በመቶው ለምግብ ፍጆታ ይውላል።

ከእነዚህ ወጪዎች መካከልም ጤፍ 57 ነጥብ 7 በመቶ በመያዝ ቀዳሚ ደረጃን የሚይዝ ሲሆን፤ ስንዴ፣ ቀይ ሽንኩርት እና ድንች በቅደም ተከተል ከ2ኛ እስከ 4ኛ ደረጃን ይይዛሉ። በርበሬ፣ ወተት፣ ዘይት፣ ሥጋ፣ እንቁላል እና ስኳርም በመዲናዋ በጣም ተፈላጊ የምግብ ሸቀጦች ናቸው።

ከምግብ ምርቶቹ ምንጭ አንጻር የመዲናው ሕዝብ በብዛት የሚጠቀማቸው የምርት አይነቶች፤ ከጤፍ የአደዓ፣ ከስንዴ የአቡሴራ፣ ከቀይ ሽንኩርት የሸዋሮቢት፣ ከዳልጋ ከብት የሐረር፣ ከምግብ ዘይት የማሌዥያ፣ ከስኳር የሕንድ ቀዳሚ ደረጃ ላይ መሆናቸውን አቶ እንዳለ አብራርተዋል። ለዋጋ ንረቱ እንደ ምክንያት የተጠቀሱትን ችግሮች በመግታት ያሉትን ምርቶች በአግባቡ መጠቀም እንዲሁም ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ካልተቻለ አሁን እየታየ ያለው እጥረት በእጥፍ እንደሚጨምር በጥናቱ ተለይቷል ይላሉ።

ጥናቱ የከተማዋ ህዝብ የምግብ ምርቶችን ከመጠቀም አንጻር የሰብል ምርቶች 48 በመቶ፣ አትክልትና ፍራፍሬ 29 በመቶ፣ እንስሳት 7 በመቶ እና የኢንዱስትሪ ምርቶች 16 በመቶ እንደሆኑ አመላክቷል። ጥናቱ በዋናነት በመዲናዋ የሚዘወተሩ የምግብ ፍጆታዎች መጠንና አቅርቦትን እንዲሁም የምግብ ፍጆታዎቹን ምንጮች በውል በመለየት የምግብ አቅርቦቱ የሚጨምርበትን የመፍትሔ ሀሳብ ያመላከተ መሆኑንም አቶ እንዳለ አንስተዋል።

አልጣጣም ያለውን የምግብ ፍላጎትና አቅርቦት ለማጣጣም እንዲሁም እየተባባሰ የመጣውን የዋጋ ንረት ለመከላከል ያለመው የትንበያ ጥናት ከ2015 እስከ 2025 ዓ.ም ያለውን ጊዜ የሚዳስስ መሆኑን አቶ አደም ይናገራሉ፤ ጥናቱ የህዝቡን ችግር ከመፍታት አንጻር አይነተኛ ሚና የሚኖረው መሆኑን ሲያስረዱ፤ በከተማ ውስጥም ሆነ በአገር እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ የምግብ ዋጋ ጭማሪ እየታየ ገልጸው፣ በአገር ውስጥ ብሎም በአዲስ አበባ ከተማ እየታየ ላለው የምግብ ዋጋ ጭማሪ መነሻውን በመለየት መፍትሔ ለመስጠት ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ጥናት መካሄዱ ጠቃሚ መሆኑን አስታውቀዋል። ጥናቱ አንጻራዊ በሆነ መንገድ የምግብ ዋጋ ንረትን፣ የአቅርቦትና ፍላጎት አለመጣጣምን ለመቆጣጠር ፋይዳው የጎላ እንደሚሆን ያላቸውን እምነትም ገልጸዋል።

አሁን ላለው የዋጋ ንረት የምርት እጥረት ችግር ብቻ ምክንያት እንዳልሆነም ጠቅሰው፣ የአገሪቱ ምርቶች ወደ ከተማዋ ገበያ ነጻ በሆነ መንገድ ወደ መግባት እንዳልቻለም ተናግረዋል። በተለያዩ ምክንያቶች ማለትም በሰላምና ጸጥታ መደፍረስ እንዲሁም ረዘም ያለ የግብይት ሰንሰለትም በምርት እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደራቸውን ይገልጻሉ።

አቶ አደም ከአዲስ አበባ ከተማ በአራቱም አቅጣጫዎች የሚመጣው ምርት በቀጥታና ጤናማ በሆነ መንገድ ወደ ከተማዋ መግባት እንደሚኖርበት ጠቅሰው፣ ምርቱም ባጠረ የግብይት ሰንሰለት መግባት እንዲችል በህገወጥ ደላሎችና በሌሎችም የሚፈጠሩ ችግሮችን ለመፍታት የንግድ ስርዓቱን ቀልጣፋ በማድረግ ቁጥጥሩንም ጠንካራ ማድረግ የግድ መሆኑን አስገንዝበዋል።

የንግድ ስርዓትን ቀልጣፋ፣ ቁጥጥሩንም ጠንካራ ከማድረግ ባለፈ ቢሮው የዋጋ ንረቱን ለመቀልበስ በዩኒዬኖችና በሸማቾች አማካኝነት ለሸማቹ ማኅበረሰብ የሚያቀርባቸውን ምርቶች አጠናክሮ መቀጠል ያለበት መሆኑን ተጠቁሟል። አቅርቦቱን ለመጨመርም ከአምራቾች ጋር እየሠራ እንደሆነና ወደ ማምረት የመግባት እቅድ እንዳለውም አቶ አደም ጠቁመዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ ጥናቱ እንዲካሄድ በተነሳሽነት የተሳተፈ ቢሆንም በጥናቱ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢፌዴሪ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ የአዲስ አበባ ስትራቴጂክ ቡድንና የኢትዮጵያ ስታስቲክስ አገልግሎት ባለስልጣን መሳተፋቸውንም አቶ አደም ገልጸዋል። ጥናቱ በዋናነት የምርት አቅርቦት እንዲበረታታ እንደሚያስችል ጠቅሰው፣ ለተግባራዊነቱም የፋይናንስ አቅርቦት አለመኖር እንቅፋት እንዳይሆን መደገፍ የሚያስፈልግ መሆኑን ተናግረዋል።

በጥናቱ የተመላከቱት መፍትሔዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት እና ፈጻሚዎች በቅንጅት መሥራትና ኃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣት እንዳለባቸው አቶ አደም ይገልጻሉ፤ ለዚህም ጊዜ፣ እውቀት፣ ከፍተኛ ልፋትና ብቃት ላለው አመራር መስጠትን ይጠይቃል። ለጥናቱ ተግባራዊነት ሁላችንም በቅንጅት መነሳት የግድ ይለናል ያሉት አቶ አደም፣ የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮም ጥናቱን ተግባራዊ ለማድረግ ተቆጥረው የተሰጡትን ኃላፊነቶች የማስተባበር ኃላፊነቱን ለመወጣት ይረባረባል ሲሉ ተናግረዋል። መንግሥት የምግብ ዋጋ ንረትን ለመከላከል የሚሰራቸው ሥራዎች እንዲሳኩ የከተማዋ ነዋሪዎችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት መንግሥት የሚያስቀምጣቸውን አቅጣጫዎች ለመፈጸም የበኩላቸውን ኃላፊነቶች መወጣት እንዳለባቸው አስገንዝበዋል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## የመንግሥት ባለሥልጣን የግድ ድሃ መሆን አለበት?

**ዋስልኝ አዬለ**

ሙስና አጀንዳ በሆነ ቁጥር አንድ ተደጋግሞ የሚነሳ ነገር አለ፤ የመንግሥት ባለሥልጣናት የሀብት መጠን ይለካል የሚል። ከጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ የፓርላማ ንግግር ዕለት ጀምሮ ዛሬ ድረስ ሙስና የመገናኛ ብዙኃኑ አጀንዳ ሆኗል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የአማራ ክልል ደግሞ የሀብት መጠናቸው ከገቢያቸው በላይ የሆኑት ላይ ምርመራ ይደረጋል በማለቱ ዜናው ሲዘዋወር ነበር።

የኔ ትዝብት ለምን ምርመራ ይደረግባቸዋል? የሚል አይደለም። ዘርፈው የከበሩ የትኛውም ባለሥልጣናት ተገቢውን ቅጣት ማግኘት አለባቸው። ይህ ሙስናን የመታገል አጀንዳ ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት እና ሁላችንም ከመንግሥት ጎን ቆመን ልንተባበረው የሚገባ ነው።

የኔ ትዝብት ከመንግሥት ባለሥልጣናት የሀብት መጠን ጋር ተያይዞ በቀልድም ሆነ በቁም ነገር የሚነሱ ልማዳዊ አመለካከቶች ላይ ነው። መንግሥት የራሱ መለኪያ እና መመርመሪያ መንገድ ስላለው ሙሰኛን የሚያጣራበትን መንገድ ለራሱ እንተወው።

ዳሩ ግን የብዙዎቻችን ልማዳዊ አመለካከት የመንግሥት ሠራተኛ ሲባል የግድ ድሃ እና ቀጫጫ መሆን ያለበት ይመስለናል። ምንም የሌለው ድሃ ነው ከተባለ እንደ ትክክለኛ የሕዝብ አገልጋይ ሀቀኛ ነው የሚታይ። በተቃራኒው የራሱ ውድ መኪና ያለው፣ ሰውነቱ ወፈር ያለ ከሆነ ‹‹ከሕዝብ ዘርፎ›› ነው የሚባል። ሰውየው መለካት ያለበት የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ከመወጣትና ከሙስናም የጸዳ መሆኑን በማወቅ እንጂ በአካላዊ ሰውነቱ እና በሚገለገልባቸው ነገሮች የጥራት ደረጃ መሆን የለበትም።

አንድ የመንግሥት ባለሥልጣን በልጆቹ፣ በወንድሞቹም ሆነ በየትኛውም የቅርብ የቤተሰብ አባል አማካኝነት ብልጥ የቢዝነስ ሰው ከሆኑ ሀብታም መሆን አይችልም? ትልቅ ንግድ ቤት ቢከፍት ለሕዝቡስ ሆነ ለአገሪቱ ገጽታ አይጠቅምም?

ከመንግሥት ባለሥልጣንነት ውጭ ያሉ ነጋዴዎችን የተነሱበትን ነገር በጣም እናደንቃለን። በየመገናኛ ብዙኃኑ ዝናቸው ይነገርላቸዋል። ከ200 ብር ተነስቶ ነው፣ ከዶሮ ተነስቶ ነው፣ ቆሎ ከመሸጥ ተነስታ ነው... እየተባለ ይመሰገኑበታል። ከትንሽ ነገር ተነስቶ ትልቅ ደረጃ ላይ መድረስ የሚያስመሰግን ስለሆነ ማለት ነው።

ታዲያ እንዲህ ከሆነ በሺዎች የሚቆጠር ደሞዝ የሚያገኝ አንድ ባለሥልጣን ጎበዝ የቢዝነስ ሰው ከሆነ ሀብታም መሆን አይችልም ወይ? እንዲያውም የሚያገኘውን ደሞዝ፣ አበልና ሌሎች ጥቅማጥቅሞች ውስኪ ከሚራጭበት ወደ ቢዝነስ ቢቀይረው ለአገርም ይጠቅማል።

የዩኒቨርሲቲ ተማሪ እያለሁ ሁላችንንም ፈገግ ያሰኘ አንድ የክፍል ጓደኛችን የተናገረው ነገር ትዝ አለኝ። ፈለግ ያሰኘን ቀልድ ሆኖ ሳይሆን የልጁ አስተያየት ከሁላችንም ለየት ያለ አተያይ ስለነበር ነው። ነገሩ እንዲህ ነው።

የሆነ ‹‹አሳይመንት›› ተሰጠን። የተሰጠን ሥራ በግቢው ውስጥ አስገራሚ ሕይወት ያላቸውን ሰዎች ወይም አስተማሪ የሆነ የሕይወት ታሪክ ያላቸውን ፈልጎ በቃለ መጠይቅ የሕይወት ታሪካቸውን መሥራት ነው። ዕቅዱ ተሰጥቶን ያገኘናቸውን ሰዎች ይሆናሉ አይሆኑም የሚለውን ለመምህራችን እያቀረብን ከመምህሩም ከተማሪውም አስተያየት እየተሰጠበት ነው።

አንደኛው ቡድን ያቀረበው በግቢው ውስጥ ለበርካታ ዓመታት ከአትክልተኛነት ጀምሮ በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ሲያገለግሉ የቆዩ ሽማግሌ ናቸው። የተመረጡበት ምክንያትም ለበርካታ ዓመታት አገልግለው በከፍተኛ ድህነት ውስጥ እየኖሩ መሆኑ ነው። ይሆናል አይሆንም በሚለው ላይ ተወያዩበት ተባልን።

አሳይመንትነቱን ልተወውና በሰውየው ሕይወት ላይ የሁላችንም ሀሳብ ተመሳሳይ ነበር። ይህን ያህል ዓመት ዩኒቨርሲቲውን ያገለገሉ ሰውየ እንዲህ መቸገር የለባቸውም፤ ዩኒቨርሲቲው ቤትም ሊሰጣቸው ይገባል አልን።

ይህኔ አንደኛው ልጅ (ሁሌም እንደመፈላሰፍ ያደርገዋል) እጁን አወጣና አስተያየት መስጠት ጀመረ። ‹‹የእኚህን ሰውየ የሕይወት ታሪክ ስትሰሩ የቁጠባ ባህላቸውንም ጠይቋቸው፤ ይህኔ እልም ያሉ ሰካራም ቢሆኑስ? ገንዘባቸውን ያባከኑት በመጠጥና በሌሎች አልባሌ ነገሮች ቢሆንስ? ዩኒቨርሲቲው እኮ እንደማንኛውም ሰራተኛ ይሆናል የከፈላቸው፤ እና እርሳቸው አባካኝ የሆኑ እንደሆነ ዩኒቨርሲቲው ምን ያድርግ?›› አለ። በወቅቱ ብንስቅም እየቆየ ሲሄድ ግን ‹‹እውነቱን እኮ ነው›› ማለትም ጀመርን።

ሽማግሌውን ታታሪ ሰራተኛ እና የግቢው ከፍተኛ ባለውለታ ያደረግናቸው ስለተቸገሩ ሳይሆን አይቀርም። ብዙ ጊዜ ልብ ብላችሁ ከሆነ በምኞት ውስጥ ያለ ሰው ምንም ያህል ለተቋምና ለአገር ውለታ ቢውል ተመስጋኝነቱ ትንሽ ነው። ተመችቶት የሚኖር ሰው የሚሰደበውና የሚወቀሰው ይበልጣል። በአንፃሩ ተቸግሮና ተጎሳቁሎ የሚኖር ደግሞ ሰነፍ ቢሆን እንኳን ተመስጋኝ ነው። ነገሩን ካየነው ግን የሥራ ትጋት ስለተቸገሩ ብቻ ላይሆን ይችላል። ምክንያቱ ደግሞ ሀብት ያላቸው ሰዎች ከህዝብ አጭበርብረው ነው ያገኙት የሚል እሳቤ ስላለ ነው።

አሁንም ደግሜ የማሳስበው ነገር ሌብነትን እያበረታታሁ አይደለም። ዳሩ ግን የአንድ ሰው ጎስቋላ ሕይወት መኖር በራሱ የሰውየውን ሀቀኝነት አያሳይም ነው። በተመሳሳይ የሰውየው ምቹ ኑሮ መኖርም ሌብነቱን አያሳይም ነው። አንድ ትልቅ ባለሥልጣንም ሆነ የቀበሌ ኃላፊ የሚጠቅመኝ የምፈልገውን አገልግሎት በፍጥነት እንዳገኝ ካስደረገልኝ፣ አግባብነት የሌለው ክፍያ እንዳልከፍል የሚያደርግ ሥርዓት ከዘረጋልኝ እንጂ የራሱ መጎሳቆል አይደለም የሚጠቅመኝ።

እንደማንኛውም ሰው በታክሲ እየሄደ፣ ተራ ምግብ ቤቶች ውስጥ እየተመገበ፣ ዝቅተኛ ዋጋ ያላቸውን አልባሳት እየለበሰ፤ ዳሩ ግን የሚመራው መስሪያ ቤት ጉዳዬን የሚያዝረከርክብኝ ከሆነ፣ መክፈል የሌለብን ገንዘብ የሚያስከፍለኝ ከሆነ፤ ይህ ሰውየ ሥልጣኑን በአግባቡ አልተወጣም ነው የሚባለው!

ከላይ የጠቀስኳቸውን የሕዝብ አገልግሎቶች በአግባቡና በፍጥነት እንዲያገኝ የሚያደርግ ሥርዓት ከፈጠረልኝ በራሱ ገንዘብ ለምን ቁርስ ቢሸፍቱ፣ ምሳ ባህርዳር፣ እራት ሐዋሳ እየሄደ አይበላም።

በእርግጥ በሕዝብ ገንዘብ (በመስሪያ ቤቱ በጀት ማለት ነው) የሚያደርገው ከሆነ ነውር ብቻ ሳይሆን በህግም የሚያስጠይቅ ጥፋት ነው። ዳሩ ግን በራሱ (ከኪሱ ማለት ነው) በሚያደርገው መዘነጥም ሆነ መመገብ ኃላፊነቱን በአግባቡ ከመወጣቱ በላይ መሆን የለበትም።

በሌላ በኩል ሁልጊዜ ሽር ሽር እና ሁልጊዜ ቅንጡ ሕይወት ፍለጋ ብቻ ከሆነ ምናልባትም ሥራ ሊበድልም ይችላል፤ የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ከሚወጣበት ሰዓት ላይ ይሽራረፋል ማለት ነው። ስለዚህ በራሱ ገንዘብም ቢሆን ከሥራ ሠዓቱ ላይ የግል ፍላጎቱን ለማሟላት መንቀሳቀስ የለበትም።

ከዚያ ውጭ ግን የሀቀኝነት እና የታታሪ ሰራተኛነት መገለጫው ድሃ መሆን አይደለም፤ ይሄ ድህነትን ማበረታታት ነው። መንግሥትም ሆነ ሕዝብ ሙስናን መከላከል ሲያቅተው ሰዎች ለፍተው ያገኙትን ነገር ሰርቀው ነው ብሎ መጠርጠር ስንፍና ነው። ምናልባትም የሕዝብን ንብረት እየመዘበረ ድሃ የሚሆን ባለሥልጣንም ይኖራል።

ስለዚህ ከመንግሥትም ሆነ ከሕዝብ የሚጠበቀው ሙስናን መከላከል፣ ሥርዓቱን ማስተካከልና ተጠያቂነትን ማስፈን እንጂ ንግድ ቤት ያለውን ሁሉ እንደ ሌባ ማየት አይደለም፤ ይህ ልማዳችን ሊቀረፍ ይገባል!

# ዓለም አቀፍ

## መንግሥትን በመቃወሙ የሞት ፍርድ የሚጠብቀዉ ኢራናዊ ራፐር

**በጋዜጣዉ ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡ የአገሪቱን መንግሥት የሚቃወሙ ሰልፎችን በመደገፉ ምክንያት በሙስና ወንጀል የተከሰሰዉ ታዋቂዉ የኢራን ራፐር በሞት ሊቀጣ እንደሚችል ቢቢሲ ዘገበ፡፡

የ31 ዓመቱ የኢራኑ ራፐር፤ ቱማጅ ሳሌይሂ ፕሮፓጋንዳን በማሰራጨት፣ ከጠላት አገር ጋር በመተባበር እና ግጭትን በማነሳሳት ተጠርጥሮ ክስ እንደተመሰረተበት አንድ የኢራን ፍርድ ቤት ባለስልጣን አስታዉቀዋል።

ቱማጅ ሳሌይሂ፤ ከአንድ ወር በፊት በተቃውሞ ሰልፎች ላይ ሲሳተፍ የሚያሳይ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሕበራዊ ሚዲያ ካሰራጨ በኋላ ነበር በቁጥጥር ስር የዋለው ሲሆን ከወራት በፊት ማሻ አሚኒ የተሰኘች ወጣት የኢራንን ጥብቅ የሂጃብ ግዴታ ጥሳለች በሚል በፖሊስ ቁጥጥር ስር እያለች ሕይወቷ ማለፉን ተከትሎ የተቀሰቀሰውን ተቃውሞ የሚደግፍ የራፕ ሙዚቃ ሰርቶ ለህዝብ ማድረሱም ተገልጿል፡፡

በዚህ ተቃውሞም ጋር ተያይዞ እስካሁን ድረስ 451 ሰዎች ህይወታቸውን እንዳጡ ትኩረቱን በኢራን ላይ አድርጎ የሚሰራው የሰብአዊ መብት ተቋም ይፋ ማድረጉ የተገለጸ ሲሆን ከ 18 ሺ በላይ ሰዎች በቁጥጥር ስር ዉለዋል።

ራፐሩ በቁጥጥር ስር ከመዋሉ ከቀናት በፊት ከአሜሪካው ሲቢሲ ጋር ባደረገው ቆይታ "የተቃውሞ ቪዲዮዎችን ማጋራት በተለይም የአገዛዙ ኢላማ እንደሚያደርጉ እና ይህም ከባድ ነው" ሲል ገልጾ ነበር።



**ቱማጅ ሳሌይሂ**

አክሎም ኢራናውያን በጣም አስከፊ ሁኔታ ውስጥ እንደሚገኙ እና "ኢራናውያን ስልጣኑን፣ ገንዘቡን ብሎም የጦር መሳሪያውን ለማስጠበቅ ሲል ካስፈለገ ሙሉ ሕዝቡን ለመግደል ዝግጁ ከሆነ የማፊያ አገዛዝ ጋር ተጋፍጠዋል" ሲልም ተናግሮ ነበር።

ከአንድ ወር በፊት ራፐሩ በቁጥጥር ስር ሲውል የሚያሳየውን ቪዲዮ የኢራን ብሔራዊ ሚዲያ አስተላልፎት ነበር። በቪዲዮው ላይ ሳሌይሂ ነኝ ያለ እና አይኑ በጨርቅ የተሸፈነ ግለሰብ ተንበርክኮ በሚንቀጠቀጥ ድምጽ የኢራን የጸጥታ ሃይሎች እንዲያመልጡ በተቃውሞ ሰልፍ ወቅት መናገሩ ጥፋት እንደሆነ ሲናገር ይደመጣል።

ሃሳብን በነጻነት በመግለጽ መብት ላይ አተኩሮ የሚሰራው አርቲክል 19 የተሰኘው ተቋም ሳሌይሂ ተገዶ የእምነት ክህደት ቃሉን መስጠቱን ተቃውሟል።

## ለአፍሪካ 5 ቢሊዮን ዶላር ማካካሻ ድጋፍ ሊሰጥ ነው

**በጋዜጣዉ ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡ በሻርም አል ሼኩ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአየር ንብረት ለውጥ ኮንፈረንስ ላይ አያላን አገራት ለአየር ንብረት ለዉጥ ተጋላጭ ለሆነችዉ ለአፍሪካ 5 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ማካካሻ ድጋፍ ለማድረግ መስማማታቸዉ አል አፍሪካ ድህረ ገጽ አስነብቧል።

ይህ ዉሳኔ ይፋ የተደረገዉ ከከፍተኛ ድርድር በኋላ መሆኑን የገለጸዉ ዘገባዉ፤ በተለይ ድጋፉ ለአፍሪካ ከተሞች የመጠጥ ዉሃ አቅርቦት የሚዉል ሲሆን በአየር ንብረት ሳቢያ ለሚደርስባቸው 'ኪሳራ እና ጉዳት' ማካካሻ የሚሆን የገንዘብ ድጋፍ በዚህ መልኩ መታሰቡ ታሪካዊ ተብሎለታል።

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሃፊ አንቶኒዮ ጉቴሬዝ ከግብፅ ሻርም ኤል ሼክ ባስተላለፉት የቪዲዮ መልእክት "ይህ ጉባዔዉ ለፍትህ ወሳኝ እርምጃ ወስዷል። ኪሳራ እና ጉዳቱን ለማካካስ ድጋፉ በሚቀጥሉት ጊዜያት ተግባራዊ ለማድረግ እንደሚጀምር ሙሉ እምነቴ ነዉ"ብለዋል። በአየር ንብረት ቀዉስ ሰለባ የሆኑ ድምጾችም በትኩረት ሊደመጡ እንደሚገቡም አስምረዉበታል።

ዋና ፀሃፊዉ፣በማደግ ላይ ያሉ አገራት ለአየር ንብረት አደጋ በጣም ተጋላጭ የሆኑትን ነገር ግን ለአየር ንብረት ቀውሱ ብዙም አስተዋፅዖ ያላደረጉ አገራትን ለማካካስ ለኪሳራ እና ለጉዳት ፈንድ እንዲቋቋም ጠንከር ያለ እና ተደጋጋሚ ጥሪ አቅርበዋል።

በጉባኤው ትልቅ አጀንዳ የሆነዉ ሌላኛዉ ጉዳይ ደግሞ የአፍሪካ ከተሞች የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ችግር ነዉ። የአለም ሪሶርስ ኢንስቲትዩት እና በአጋር አካላት እ.ኤ.አ. በ2032 ለ100 የአፍሪካ ከተሞች ለመጠጥ ዉሃ አቅርቦት የሚዉል 5 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ለመመደብ ስምምነት ላይ ደርሰዋል።

በስምምነቱ መሰረት የከተማ አመራሮች የተቀናጀ የዉሃ አስተዳደር፣ የተፋሰስ አስተዳደር፣ የንፅህና አገልግሎትን ማሳደግ፣ የተሻሻለ የዝናብ ውሃ አያያዝ እንዲሁም የተበከለ ውሃ አያያዝን ጨምሮ የተለያዩ የውሃ ጉዳዮችን ለመፍታት የሚያስችላቸዉ ለማድረግ የገንዘብ እና የቴክኒክ ድጋፍን በቀጥታ ማግኘት ይችላሉ።

አንቶኒዮ ጉቴሬዝ፤ የአየር ንብረት ለዉጥ ሁኔታ የ1 ነጥብ 5 ዲግሪ ሴልሺየስ ገደብ ተግባራዊ በማድረግ የሰዉ ልጅን ከአየር ንብረት አደገኛ ቀዉስ መታደግ እንደሚያስፈልግ የፓሪስ ስምምነት ሁሉም እንደገና እንዲያጤን አዉስተዋል። የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ኃላፊ ለኪሳራ እና ለጉዳት የሚውል ፈንድ አስፈላጊ ቢሆንም በአየር ንብረት ለዉጥ ምክንያት አፍሪካ ወደ በረሃ የሚቀይር ተግባር ከተፈጸመ ድጋፍ ብቻዉን ትርጉም አልባ መሆኑንም አስገንዝበዋል።

በአህጉረ አፍሪካ ከከሰል ድንጋይ የሀይል አማራጭ ወደ ታዳሽ ሀይል ለማሸጋገር ለመሰረተ ልማት ግንባታዉ የሙያዉ 66 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንደሚያስፈልግ የተናገሩት ዋና ፀሃፊዉ፤ የኢንቨስትመንት እና የውሃ ምንጮችን ለማጎልበት በዓመት ከ9-14 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንደሚያስፈልግም ጠቁመዋል።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

# ረቡዕ ስፖርት
አዲስ ዘመን

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# ለተሰንበት ግደይ- በአዲስ ርቀት ለአዲስ ክብረወሰን ተዘጋጅታለች

ብርሃን ፈይሳ

42ኛው የቫሌንሲያ ማራቶን እሁድ ይካሄዳል። በስፔን ከሚካሄዱ የአትሌቲክስ ውድድሮች ሁሉ ተወዳጅ የሆነው ይህ የጎዳና ላይ ሩጫ ከከተማዋ የቦታ አቀማመጥ ጋር በተያያዘ ፈጣን ሰዓት ለማስመዝገብ ምቹ በመሆኑ በአትሌቶች ዘንድ ተመራጭ ነው። በማራቶን ታዋቂ አትሌቶች ተሳታፊ ሲሆኑ፤ በ10 ኪሎ ሜትር በሚካሄደው ህዝባዊ ሩጫ ደግሞ 30ሺ ሰው ተሳታፊ እንደሚሆንም ታውቋል።

በዓለም አትሌቲክስ የወርቅ ደረጃ ከተሰጣቸው የጎዳና ላይ ሩጫዎች መካከል አንዱ በሆነው በዚህ የሩጫ ውድድር ላይም ኢትዮጵያውያንን ጨምሮ የርቀቱ ዝነኛ አትሌቶች እንደሚፎካከሩ አረጋግጠዋል። በአትሌቲክስ ቤተሰቡ በተሰጠው ቅድመ ግምት መሰረትም ውድድሩ በኢትዮጵያውያን አትሌቶች የበላይነት ይጠናቀቃል በሚል የሚጠበቅ ሆኗል። በተለይ በሴቶች መካከል በሚካሄደው ውድድር ኢትዮጵያዊቷ ወጣት አትሌት ለተሰንበት ግደይ ተሳታፊነቷን ማሳወቋ በውድድሩ አዲስ ነገር እንዲጠበቅ ምክንያት ሆኗል።

በ5 ሺ እና 10ሺ ሜትር እንዲሁም በ15 ኪሎ ሜትር የዓለም ክብረወሰን ባለቤት የሆነችው ለተሰንበት አሁን ደግሞ ከምትታወቅበት የመም ውድድር ወደ ማራቶን ፊቷን ያዞረችበት ውድድር ሆኗል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በጎዳና ላይ ውድድሮች የታየችው አትሌቷ ባለፈው ዓመት በዚሁ የቫሌንሲያ ግማሽ ማራቶን ሮጣ 1:02:52 በሆነ ሰዓት በመግባት የርቀቱን የዓለም ክብረወሰን በእጇ አስገብታለች። አሁን ደግሞ በረጅሙ ርቀት ማራቶን ልትወዳደር መዘጋጀቷን ግሎባል ስፖርት ኮሚዩኒኬሽን የተሰኘው የስልጠና ቡድኗ አስቀድሞ ነበር ያሳወቀው። ይህንን ተከትሎም የአትሌቷ አሰልጣኝ ኃይሌ እያሱ ከለተሰንበት ጋር ከዓመታት በፊት በ5ሺ ሜትር እና 10ሺ ሜትር እስከ ማራቶን የዓለምን ክብረወሰን መስበር የሚል እቅድ እንደነበራቸው ገልጾ ነበር። በዚህ መሰረት አትሌቷ አሁን በደረሰችበት ማራቶን አዲስ ነገር ልታስመለክት ትችላለች በሚል ትጠበቃለች።

ለተሰንበት ዝግጅቷን አስመልክታም በስልጠና ቡድኗ በኩል አስተያየቷን ገልጻለች። ዝግጅቷን በአዲስ አበባ ስታደርግ ቆይታ ያጠናቀቀች ሲሆን፤ በሳምንት ለአንድ ቀን 30ኪሎ ሜትር በመሮጥ ርቀቱን እንደተላመደችውም ጠቅሳለች። አሰልጣኟም ማራቶንን መሮጥ እንደምትችል አረጋግጦላታል። የመጀመሪያውን የዓለም ክብረወሰን በ5ሺ የሰበረችው በቫሌንሲያ በመሆኑ በቦታው የተለየ ትውስታ ያላት አትሌቷ ሌላኛውን ህልሟን ለማሳካትም ደግሞ በተመሳሳይ ከተማ ማራቶን ትሮጣለች።

በቫሌንሲያ ማራቶን የሴቶች ሩጫ ከዚህ ቀደም ዘጠኝ የሚሆኑ አትሌቶች አሸናፊ ሊሆኑ ችለዋል። ባለፉት ሁለት ዓመታት የበላይነቱን የያዙት ኬንያዊያን አትሌቶች ሲሆኑ፤ የቦታው ፈጣን ሰዓትም እአአ በ2020 ፔሬስ ጄፕቺርቺር 2:17:16 የተመዘገበ ነው። በዚህ ውድድም ለመጀመሪያ ጊዜ ተካፋይ የምትሆነውና ክብረወሰን በመስበር ልምድ ያላት ብርቱዋ አትሌት ለተሰንበት አዲስ ሰዓት ታስመዘግባለች በሚል ትጠበቃለች። ሱቱሜ ከበደ፣ ቲኪ ገላና፣ ትዕግስት ግርማ፣ እታገኝ ወልዱ፣ አማኔ ሻንቁሌ፣ ታደለች በቀለ እና ብሩክታይት እሸቱ ደግሞ ከለተሰንበት ጋር የሚሮጡ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ናቸው።



ብርቱዋ አትሌት ለተሰንበት ግደይ የመጀመሪያ የማራቶን ተሳትፎዋን ታደርጋለች፤

በወንዶች በኩል ደግሞ ርቀቱን ከ2 ሰዓት ከ05 ደቂቃ በታች የሮጡ ሰባት ያህል አትሌቶች ተካፋይ ይሆናሉ። በውድድሩ ተሳታፊ ከሆኑ አትሌቶች ፈጣን ሰዓት ያለው አትሌት ጌታነህ ሞላ ሲሆን፤ በርቀቱ ያስመዘገበው 2:03:34 የሆነ ሰዓት ቀዳሚው ነው። በአምስት ሰከንዶች ብቻ ከእሱ ያነሰ ሰዓት ያለው ታምራት ቶላም ተጠባቂ አትሌት ነው። የኦሪጎኑ የዓለም ማራቶን ቻምፒዮና የሆነው አትሌቱ በማራቶን ከፍተኛ ልምድ አለው። በዚህ ዓመት በተካሄደው የቶኪዮ ማራቶንም ሶስተኛ ደረጃን በመያዝ ነበር ውድድሩን ያጠናቀቀው። 2:04:27 የሆነ ሰዓት ያለው ሌላኛው ኢትዮጵያዊ አትሌት ዳዊት ወልዴ ደግሞ ሶስተኛው ባለፈጣን ሰዓት ነው።

በአምስት ሰከንዶች ብቻ በመዘግየት አራተኛ ደረጃ ላይ የተቀመጠው አትሌት ደግሞ ጆናታን ኮሪር ነው። አትሌቱ ለኢትዮጵያውያኑ ፈተና እንደሚሆን ቢገመትም፤ ህዝቂል ተወልደ፣ ጫሉ ዴሶ እና ወርቅነህ ታደሰን የመሳሰሉ አትሌቶች ግን በቀላሉ እጅ የሚሰጡ አይሆኑም።


## 2ተኛ ዙር የወጣ
## ግልጽ የግዢ ጨረታ ማስታወቂያ

በኦሮሚያ ክልል አስተዳደር በባሌ ዞን የሮቤ ከተማ ገንዘብ ጽ/ቤት ለ 2015 የበጀት ዓመት 2+ኛ ዙር ግዢ ለሮቤ ከተማ ሴክተር መስሪያ ቤቶች አገልግሎት የሚውሉ ፤

**- CCTV Camera በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡**

**በዚሁ መሰረት የሚከተለውን መስፈርቶች የሚያሟሉ ተጫራቾች መወዳደር የሚችሉ መሆኑን እንገልጻለን::**

1. የዘመኑ የታደሰ ንግድ ፍቃድ ያለው የዘመኑን ግብር ከፍሎ ያጠናቀቀና ከገቢዎች ጽ/ቤት ክሊራንስ ማቅረብ የሚችሉ፡፡
2. ተጨማሪ እሴት ታክስ የሚመለከተው ከሆነ የተመዘገበበትን ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፡
3. ተጫራቾች የጨረታውን ሠነድ ዋናውንና ኮፒ በታሸገ ኤንቨሎፕ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
4. ተጫራቾች የጨረታውን ሠነድ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ15 ተከታታይ የስራ ቀናት የማይመለስ ብር 200.00 (ሁለት መቶ) ሮቤ አገር ውስጥ ገቢ ጽ/ቤት በመክፈል ሰነዱን ከሮቤ ከተማ ገንዘብ ጽ/ቤት መግዛት ይችላሉ፡፡
5. ተጫራቾች የሚያቀርቡት እቃ ጥራቱ የተረጋገጠ መሆኑን ማስረጃና በተጨማሪ ይጠቅመኛል የሚሏቸው ማስረጃዎች ከሉ ማቅረብ ይችላሉ፡፡
6. ጨረታው ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት በ 16ኛው ቀን 2015 ዓ.ም ከጠዋቱ 3:30 ሰዓት ተዘግቶ በ4:00 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡ ዕለቱ በአል ወይም ዝግ ከሆነ በቀጣዩ የሥራ ቀን ጨረታው ይከፈታል፡፡
7. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ (CPO) ከታወቀ ባንክ 10.000.00 /አስር ሺህ/ ብር ማስያዝ አለባቸው፡፡
8. መስሪያ ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡

**ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር 0226650836 |3186 / 0913091660 ደውሎ መጠየቅ ይችላሉ፡**

**የሮቤ ከተማ ገንዘብ ጽ/ቤት**



## ማስተካከያ ተደርጎ የወጣ የጨረታ ማስታወቂያ

በቁጥር 078 ቀን ህዳር 18/-2015 ዓ.ም በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አዲስ ዘመን ጋዜጣ ገጽ 27 በወጣው ግልጽ ጨረታ ጨረታው አየር ላይ የሚውልበት ቀን ያልተገለጸ ስለሆነ ማስተካከያ ተደርጎ ጨረታው እንደገና እንዲታተም እናስታውቃለን፡፡

በደቡብ/ብ/ህ/ክ/መ/በወላይታ ዞን በቦዲቲ ከተማ አስተዳደር ፋ/ጽ/ቤት በ2015 በጀት ዓመት በከተማችን በUIIDP ፕሮግራም በጀትና በከተማው አስተዳደር በጀት የሚሠራውን ሼድ ግንባታ ከቀረበው የሥራ ዝርዝርና ዲይዛይን መሠረት በቦዲቲ ከተማ ጁነር ት/ቤት አካባቢ የሳይት መለያ ቁጥር Boditi/UIIDP/CW-009/2022/23 የሆነውን 4 ብሎክ ሼድ ጨረታ እንዲወጣ በቁጥር ቦማቤ/811/2015 በቀን 06/03/2015 ዓ/ም በፃፉት ደብዳቤ ጨረታ እንዲወጣ በማለት ጠይቀውናል፡፡

**በዚሁ መሠረት፡-**

1. ተጫራቾች አግባብነት ያለውን የ2015 ዓ/ም ግብር የከፈሉበት ማስረጃ፣ በዘርፉ የታደሠ ህጋዊ የግንባታ ፈቃድ ያላቸው፣ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ያላቸው፣ የግብር መከፈያ መለያ ቁጥር ያለው ቫት ተመዝጋቢ የሆነ በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ የተመዘገቡ መሆን አለባቸው፡፡
2. ተጫራቾች በኮንስትራክሽን ዘርፍ GC-5/BC-4 እና ከዚህ በላይ መሆን አለባቸው፣
3. CPO/ባንክ ጋራንቲ/ ከታወቀ ባንክ 100,000 /አንድ መቶ ሺህ ብር/ ብቻ ማቅረብ አለባቸው
4. ተጫራቾች BID Submission sheet በአግባቡ ሞልቶ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፣
5. የጨረታ ዋጋ ማቅረቢያ ሰነድ እና ቴክኒካል ሰነድ በተለየ በማድረግ ኦርጂናልና ሁለት ኮፒ በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ አድራሻውን በመጥቀስ በመ/ቤቱ በታሸገ ሳጥን መክተት ይኖርባቸዋል፡፡ ተጫራቾች ለፋይናንሻል ግምገማ የመጀመሪያውን ቴክኒካል ግምገማ ማለፍ አለባቸው፡፡
6. ከላይ እንደገለጽነው መስፈርቶችን የሚያሟሉ ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን ይህ ማስታወቂያ ከወጣት ቀን ጀምሮ በሥራ ሰዓት ለሰነዱ የማይመለስ 300/ ሦስት መቶ ብር/ ብቻ ቦዲቲ ከተማ ገ/ባ/ቅ/ጽ/ቤት ቀርበው በመክፈል በወሰዱት ደረሰኝ ከቦዲቲ ከተማ ፋይናንስ ጽ/ቤት ግዥ ኬዝ ቲም በአካል በመቅረብ የጨረታ ሰነድ መውሰድ ይችላሉ፡፡
7. ጨረታው ከተከፈተ በኋላ ባቀረቡት የመወዳደሪያ ሀሳብ ለውጥ/ማሻሻያ ማድረግ የማይችል መሆኑን እንዲሁም ጨረታው ከተከፈተ በኋላ ከጨረታው ራሳቸውን ማግለል የማይችሉ መሆኑን፡፡
8. ጨረታው በጋዜጣው ላይ በተገለጸው ቦታ፣ ቀንና ሰዓት ይከፈታል፡፡
9. ተወዳዳሪዎች ከዚህ በፊት የሠሩበትን ማስረጃ /የመልካም ሥራ አፈጻጸም ማቅረብ ይኖርባቸዋል፣
10. ተጫራቾች የሚያቀርቡት የመወዳደሪያ ሀሳብ ስማቸውን፣ ፊርማቸውንና አድራሻቸውን ማስፈር አለባቸው
11. ግዥ ፈጻሚ አካል ወይም ጽ/ቤት ጨረታውን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፣
12. አሸናፊው ተጫራች አሸናፊነቱ ከተገለጸበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10/አስር/ ተከታታይ ቀናት ውስጥ ቀርቦ ውል መግባት ይኖርበታል፡፡ ውል ለመግባት ፈቃደኛ ካልሆነ/ውል ለመግባት የማያስችል በቂና አሳማኝ ምክንያት መኖሩን አሸናፊነቱን ከተነገረበት ቀን ጀምሮ ባሉት 5/አምስት/ ቀናት ውስጥ በህጋዊ ማመልከቻ ለአጫራች መ/ቤት የማያቀርብ ከሆነ በዚሁ ምክንያት መ/ቤቱን ለሚደርሰው ችግር ተጫራቹ ተጠያቂ ይሆናል፡፡
13. ጨረታውን ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ለ30 ተከታታይ ቀናት በአየር ላይ ከዋለ በኋላ በ ዕለቱ በ4፡00 ሰዓት ታሽጎ በ4፡30 ላይ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው እንዲሁም ታዛቢዎች በተገኙበት ይከፈታል፡፡

ጨረታው የሚከፈትበት ቀን የበዓል ቀን ወይም ሰንበት ከሆነ ለቀጣይ የሥራ ቀን በማስታወቂያው በተጠቀሰው ሰዓትና ጊዜ ይከናወናል፡፡

**በደቡብ/ብ/ህ/ክ/መ/በወላይታ ዞን**

**የቦዲቲ ከተማ አስተዳደር ፋ/ጽ/ቤት**